# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃግብር

**ሸክኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ (በሸካ ዞን ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)**


በ

ሻሼ ያዜ


አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት


ነሐሴ፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃግብር

# በሸክኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ (በሸካ ዞን ኩቢጠ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)

በ

ሻሼ ያዜ

አማካሪ፡ ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

## ማረጋገጫ

እኔ ከታች ስሜና ፊርማዬ የተቀመጠው ተማሪ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የራሴ ስራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥም የተጠቀምኳቸውን ዋቤዎች በሙሉ መጥቀሴን በግል ፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡-

ተማሪ ______________________________

ፊርማ ____________

ቀን ____________

## የፈተና ቦርድ አባላት

| የአማካሪ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| __________________________ | _________ | ____________ |
| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| __________________________ | _________ | ____________ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| __________________________ | _________ | ____________ |

# ምስጋና

በቅድሚያ ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሄር ከብዙ ችግርና ፈተና አውጥቶ ለዚህ ላደረሰኝ ምስጋና አቀርባለሁ። በመቀጠል እንድማር በማበረታታት ከጎኔ ላልተለየኝ ወንድሜ ለመምህር ባይነሳኝ ያዜ፡፡

እንዲሁም በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ትምህርት ክፍል መምህራን እና የ9ኛክፍል ተማሪዎች ለጥናቴ መረጃ በመስጠት ስለተባበሩኝ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባሁ፡፡በተጨማሪም በቁሳቁ እና በማማከር ለተባበረኝ ለመምህር ቁሜ ተዋበና ለተሰቦቼ፣ የሁለተኛ ዲግሪዬን ስማር ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ የጅማ ዩኒቨርስቲ የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የአማርኛ ተግባራዊ ስነልሳን መምህራን በሙሉ በአመቱ የትምህርት ወቅት ላደረጋችሁልኝ ድጋፍ ሁሉ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ፡፡

በተለይም ደግሞ የምርምር ጥናቴን በማንበብና አቅጣጫ በመጠቆም፣ የተበላሸውን በማስተካከል ላገዙኝ አማካሪዬ ዶ/ር ጥበቡ ሽቴ ከፍተኛ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባሁ፡፡

# አጠቃሎ


የዚህ ጥናት አብይ የትኩረት አቅጣጫ በሽክኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በሸካ ዞን ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ለዚህም የኩቢጦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለጥናቱ አመቺ ሆኖ ስለተገኘ ትምህርት ቤቱ በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ በዚሁ በተመረጠ ትምህርት ቤት ከሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በሸከኛ አፍ ፈት የሆኑ 100 ተማሪዎች እድል ሰጪ የንሞና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠው የፍጥነት ንባብ መለኪያና የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና በመፈተን ለ9ኛ ክፍል አማርኛን በማስተማር ላይ ለሚገኙ መምህራን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ መረጃ ተሰብስቧል፡፤በተጠቀሱት የመረጃ ማሰባሰቢያ የተገኙት መረጃዎች ተጠናቅረው በቅይትጥ የምርምር ዘዴ ና እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ አይነታዊ የምርምር ዘዴ በሆነው በገላጭ አተናተን ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶን በSPSS የኮምፒውተር ፕሮግራም ተሰልቷል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው  የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትውጤት ከፍተኛው አስር ከአስር(ከ10 ከ10) ሲሆን ዝቅ ተኛው ሁለት ከአስር ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም አብዛኛው ተማሪ ዝቅተኛአንብቦ የመረዳትችሎታ ላይ የሚገኝ መሆኑን አሳይቷል፡፡በጥናቱ ግኝት መሰረት ከግማሽ 50% በታች ያገኙ ተማሪወች አጠቃላይ ብዛት በአማካይ 60% ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተውአብዛኞቹ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ፈተናው ማለፊያ ውጤት እንዳላገኙ ነው፡፡በአንብቦ መረዳቱ እንድተመዘገበው ውጤት ሁሉ በጣም ከፍተኛ የሚባል (80% እና በላይ)የማንበብ ፍጥነት ውጤት ያሰመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥርም በጣም ውሱን 14 ብቻ መሆኑ የሚያመለከተው በአብዛኛው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከፍተኛ የንባብ ፍጥነት ችገር መኖሩንነው፡፡

በተጠኝዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥንት መካከል ቀጥተኛ በሆነ መንገድ አሉታዊ የሆነ ተዛምዶ እንደሚታይ ስታስቲከሳዊ መረጃው ያመለከታል፡፡ይሀም ማለት የተጠኝዎች የንባብ ፍጥነት ሲቀንስ በዚያው ልክ የአንብቦ መረዳት ችሎታም መቀነስ እንደሚያሳይ ተረጋግጣል፡፡በዚህ መሰረት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ የማንበብ ፍጥነት እና የማንበብ ብቃት በአዝጋሚ ደረጃ ላይ መገኘት ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆን እንደ አብይ ችግር ሊቆጠር የሚችል ጉዳይ መሆኑን መገመት ተችሏል፡ ፡ጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማደረግ እና በክለሳ ድርሳናት በመታገዝ የመረጃ መፍትሄ ሀሳቦች ተመላከተው ጥናቱ ተጠቃሏል፡፡

# ማውጫ

**ርእስ** **ገጽ**


ምስጋና ........ ii

አጠቃሎ ........ iii

የሰንጠረዥ ማውጫ ........ vii

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥቄያዎች ........ 4

1.4 የጥናቱ ዓላማ ........ 4

1.4.1 የጥናቱ ዓብይ ዓላማ ........ 4

1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 4

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 5

ምዕራፍ ሁለት ........ 6

ክለሣ ድርሳናት ........ 6

2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች ........ 6

2.1.1. የንባብ ምንነት ........ 6

2.1.2. የንባብ ጠቀሜታ ........ 7

2.1.3. አንብቦ የመረዳት ምንነት ........ 8

2.1.4. የአንብቦ መረዳት ክሂልን ማዳበር ........ 8

2.1.5. የንባብ ንዑሳን ክሂሎች ........ 9

2.1.6. የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፈተናዎች ........ 10

2.1.7 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች ........ 12

2.1.8 የንባብ ፍጥነት ምንነት ........ 13

2.1.9 የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ........ 14

2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 17

ምዕራፍ ሦስት ........ 19

3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 19

3.2 ተጠኚዎችና የናሙና አወሳሰድ ........ 19

3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ ........ 19
3.2.2 የክፍል ደረጃና የተማሪዎች አመራርጥ........ 19
3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራርጥ........ 20
3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ........ 20
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች........ 20
3.3.1 ፈተና........ 20
3.3.2 ቃለ መጠይቅ........ 21
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ........ 22
ምዕራፍ አራት........ 23
የመረጃ ትንተና ........ 23
4.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች........ 23
4.1.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና አንድ አንፃር........ 24
4.1.2 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና ሁለት አንፃር ........ 25
4.1.3 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ........ 26
4.2 የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ እና ፈተና ሁለት ዝርዝር መረጃ........ 27
4.2.1 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና አንድ ........ 28
4.2.2 የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና ሁለት ........ 29
4.2.3 የፈተና አንድና ሁለት አማካይ የቃላት ብዛትና የማንበብ ፍጥነት........ 30
4.3 አፍ መፍቻ ቋንቋ ከ አንብቦ መረዳት ችሎታና ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለው ግንኙነት 31
4.4 የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ ግንኙነት........ 32
4.5 የንባብ ፍጥነትና አንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ግንኙነት ........ 32
4.6 በንባብ ፍጥነጥ በአንብቦ የመረዳት መካከል ያለው ተዛምዶ ........ 33
4.7 ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና........ 34
4.7.1 የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታንና የንባብ የመረዳት ችሎታንና........ 34
የንባብ ፍጥነትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 34
4.7.2 በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የተገኙ ... Error! Bookmark not defined.
መረጃዎች ትንተና ........Error! Bookmark not defined.
4.7.3 የመምህራን ክትትልን የራስ ጥረትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ........ 36
ትንተና........ 36
ምዕራፍ አምስት........ 39

5. ማጠቃለያና አስተያየት ........................................................................................ 39
5.1 መደምደሚያ ........................................................................................................ 39
5.2 ማጠቃለያ .................................................................................................. 39
5.3 አስተያየት.................................................................................................. 41
ዋቢዎች ................................................................................................................ 42
አባሪ አንድ ............................................................................................................ 46
አባሪ ሁለት............................................................................................................ 49
አባሪ ሶስት ............................................................................................................ 53
አባሪ አራት............................................................................................................ 56
አባሪ አምስት .......................................................................................................... 59

## የሰንጠረዥ ማውጫ

**የሰንጠረዥ ርእስ** **ገጽ**


ሰንጠረዥ 1 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አንድ ውጤት ........................................ 24
ሰንጠረዥ 2 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት ውጤት ........................................ 25
ሠንጠረዥ 3፡ የተጠኝዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ አመላካች ........................... 26
ሠንጠረዥ 4፡- የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና ................................ 28
አንድ ........................................................................................................ 28
ሰንጠረዥ 5፡- የተጠኝ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና ሁለት .................................. 29
ሠንጠረዥ 6፡- የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አማካይ የንባብ ፍጥነት የሚያሳይ መረጃ ...... 30
ሰንጠረዥ 7የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ............. 32
ፍጥነት ጋርያለው ግንኙነት ............................................................................ 32
ሠንጠረዥ 8 በንባብ ፍጥነትና በአንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን
ተዛምዶየሚያሳይ ........................................................................................ 33
ሠንጠረዥ 9 ለቃለ መጠይቅ የተሳተፉ መምህራን አጠቃላይ መረጃ የሚያሳይ .............. 34

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው አላማዎች መካከል አንዱ የተማሪዎች የንባብ ክህሎት እና ልማድን ለማዳበር ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቋንቋ ትምህርቱ ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚማሯቸው የትምህርት አይነቶች ብቻ ሳይሆን ከትምህርታቸው ውጭ የሆኑ ነገሮችን የማንበብ ልምድን እንዲይዙ የማድረግ አላማም አለው፡፡ የንባብ ባህል ከትምህርት መስፋፋትና ማደግ ጋር የማይነጣጠል ትስስር አለው፡፡ በሀገራችን በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዋና ዋና አላማዎች አንዱ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ማዳበር ነው፡፡ የማንበብ ክሂል ማዳበር ማዳመጥ፣ መናገርና መፃፍ ክሂሎች መዳበር አስተዋጽኦ እንደሚኖረው Sheng (2000:12) ያብራራል፡፡

> ትምህርት ሚኒስቴር (2007፡ 7) በማንዋል እንደገለጸው በኢትዮጵያ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለማድረስ ስኬታማ ስራ ቢሰራም በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን የሚማሩ ተማሪዎች የንባብ ችሎታ ግን አስደንጋጭ መሆኑን የEGRA ጥናት ውጤት አመላክቷል፡፡ የዝቅተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ምዘና ጥናት የደቡብ ክልልን ጨምሮ በስምንት ክልሎች የተካሄደ ሲሆን የማንበብ ችሎታን በተመለከተ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማንበብ ክሂል በውስጡ በርካታ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን ይይዛል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲሆን የንባብ ፍጥነትም እንደዚሁ ነው፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የፍጥነት ንባብን በተመለከተ ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ክሂል ተያያዥ በሆነ መልኩ በአንድ ላይ መዳበር እንደለባቸውና በሽምደዳ የሚካሄድ የፍጥነት ንባብም ሆነ ከተገቢው ጊዜ በላይ የሚወስድ አንብቦ የመረዳት ሂደት እንደማይደገፉAnderson (1999:29) ይገልፃሉ፡፡ የቋንቋ ተማሪዎች እነዚህን የንባብ ንዑሳን ክሂሎች እንዲያሻሻሉ ማድረግ እንደሚቻልም ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህን ንዑሳን ክሂሎች በአንድነት ማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡

የአንባቢዎችን የአንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት በተመለከተ Fry (1963፡ 52) ሲገልፅ ከዝግተኛ አንባቢዎች ይልቅ ፈጣን አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸው እንዲጨምር ብዙ ማንበብ፣ ሀሳብን አሰባስቦ ማንብብ (መመሰጥ)፣ ጊዜን በጅቶ መጠቀም፣ ፍጥነትን ለመጨመር መለማመድ፣ ዋና ሀሳቦችን ለመረዳት ማንበብ፣ ሳቢፅሑፎችን አዘውትረው ማንበብ፣ ፍጥነትን በራስ ወስኖ ለማንበብ መዘጋጀትንና በንባብ ጊዜ ለሚነበብ ንባብ ትኩረት የመስጠት ልምድን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በማለት ያብራራሉ፡፡

የንባብ ክሂል ቋንቋን በማስተማር ሂደት ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ የዚህ ክሂል በአግባቡ መዳበር ለሌሎች ክሂሎች ማደግ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ የተሻለና ጥሩ አንባቢ ለመሆን የዳበረ የንባብ ችሎታ ያለው መሆን ያስፈልጋል፡፡ የንባብ ችሎታ ሲባል በንባብ ሂደት የምንጠቀምባቸው የተለያዩ የአነባበብ ስልቶች እና የንባብ ፍጥነታችንን ያጠቃልላል፡፡ የዳበረ የሚባለው የንባብ ችሎታም በተገቢው ፍጥነት አንብቦ መረዳትን የሚመለከት ነው፡ ፡ (Nuttal 1982:3) ከዚህ የምንረዳው አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት መገንዘብ ሲሆን በፍጥነት ማንበብ ለአንብቦ መረዳት አስተቸፅኦ እንዳለው ነው፡፡

ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች አንዱ የንባብ ችሎታን ማዳበር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የንባብ ችሎታ ሲባል የተማሪዎችን በተገቢ ፍጥነት ማንበብና አንብቦ መረዳትን ይመለከታል፡፡በአገራችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በርካታ የሆኑ የሀገራችን ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ደካማ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን በጥናት ካመላከቱት መካከል መኮንን (2000) "በአዊኛ" አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ግምገማ በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት መግለፃቸው ተሾመ (1997) በከንባታ ጠንባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት" በሚል ርዕስ እንዲሁም አያሌው (2001) በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአብብቦ የመረዳት ክሂል ጋር ያለው ተዘምዶ በወልደያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተመሰረተ ጥናት በሚል ርዕስ ባደረጉት የሁለተኛ ድግሪ ማሚያነት ጥናት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነና የተማሪዎች የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑንና አሁንም ትልቅ ችግር እንደሆነ ተገልጿል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች አንዱ የንባብ ችሎታን ማዳበር እንደሆነ ይታወቃል። የንባብ ችሎታ ሲባል የተማሪዎችን በተገቢ ፍጥነት ማንበብና አንብቦ መረዳትን ይመለከታል። በአገራችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በርካታ የሆኑ የሀገራችን ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ደካማ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን በጥናት ካመላከቱት

መካከል መኮንን (2000) "በአዊኛ" አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ግምገማ በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት መግለፃቸው ተሾመ (1997)በከንባታ ጠንባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት" በሚል ርዕስ እንዲሁም አያሌው (2001)በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአብብቦ የመረዳት ክሂል ጋር ያለው ተዘምዶ በወልደያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተመሰረተ ጥናት በሚል ርዕስ ባደረጉት የሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት ጥናት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነና የተማሪዎች የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑንና አሁንም ትልቅ ችግር እንደሆነ ገልጿል።

የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን በየጊዜው በወላጆች፣ በመምህራን፣ በተማሪዎች እና በተለየዩ ጥናት ባካሂዱት ተመራማሪዎች ይነገራል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ብለው ካሠፈሯቸው ነጥቦች መካከል የሚነበበው ፅሑፍ ሳቢና ተመጣጣኝ አለመሆን፣ ለማስተማሪያነት የተመደበው የክፍለጊዜ መጠን ማነስ፣ በየመማሪያ ክፍሎች በየክፍል ተመድበው የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር መብዛትና ለክትትል አመቺ አለመሆን፣ እንዲሁም የመምህሩ አተገባበር ዋነኛ ችግር መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ተዘውትረው ቢነሱም አሁንም ችግሩ ሙሉ በሙሉ ያልተቀረፈ መሆኑ የብዙ ምሁራን የጋራ ስምምነት ስለሆነ በዚህ ችግር ዙሪያ ጥናት ማካሄዱ አስፈላጊነቱ ምን እንደሚመስልና የችግሩም መንስኤ ምን እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ ጥናት አካሂዶ ማረጋገጥ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ አጥኝዋም ይህን ሃሳብ መነሻ በማድረግ በተጨማሪም በመምህርነት የሙያ ቆይታዋ በሸካ ዞን ኩቢጦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመድባ በማስተማር በቆየችባቸው 6 አመታት ስታስተምራቸው ከነበሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል አብዛኞቹ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት

ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን እንዲያነቡ ሲታዘዙ የሚታይባቸው የአነባበብ መደነቃቀፍ፣ ለማንበብ ፍቃደኛ አለመሆንና፣ የምንባብ ፈተና ላይ የሚታይባቸው የሰአት አጠቃቀም ችግርን አስተውላለች፡፡ በተጨማሪም፤ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ እንደ ትምህርት ቤት ቀደም የተካሄደ ጥናት አለማግኘቷ ይህን ጥናት እንድታካሂድ አነሳስቷታል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥቄያዎች

- በሸክኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ምን ይመስላል?
- በሸክኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ፍጥነታቸውና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ተዛምዶ ምን ያህል ነው?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1 የጥናቱ ዓብይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሸካ ዞን የኪ ወረዳ በ ኩቢጦ ከተማ ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል የሸክኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ይሆናል ፡፡

### 1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ ከላይ ካስቀመጠው ዓብይ ዓላማ በመነሳት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- በሸክኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ያለበትን ደረጃ መመርመር
- በሸክኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ተጠንቶ ሲያበቃ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች መካከል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት መምህራን ምን ምን እገዛ ማድረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ ያሳያል፣ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይጠቁማል ፤

በተጨማሪም ወደፊት በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ አካላት እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

አንድን ጥናት ከመነሻ እሰከ መድረሻው ለታለመለት አላማ ይበልጥ  እንዲውልና ጥናቱም ችግር ፈቺ እንዲሆን በስፋት ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ሰፋ ያሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብና መረጃ ሰጪዎችን ለማግኘት በርከት ያለ ገንዘብ ጊዜና ጉልበት ይጠይቃል;; ሰለዚህ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገዉ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ከሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንዱ በሆነው በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል የሸክኛ  አፍ ፈት ተማሪዎችን በናሙናነት በመውሰድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ላይ ተወስኗል፡፡ ሌሎች የንባብ ክሂል ትምህርት አተገባበር፤ የንባብ ክሂል የማሰተማር ስነዘዴን ንባብ ለማስተማር የሚዘጋጁ መርጃ መሳሪያዎችን አይመለከትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሣ ድርሳናት

## 2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1. የንባብ ምንነት

ስለንባብ ምንነት የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ ጊዜ የተለያየ ብያኔ የሰጡ ሲሆን የአብዛኞቹ ምሁራን ብያኔም ተመሳሳይነት አለው፡፡ ስለንባብ ምንነት ከተሰጡ ብያኔዎች መካከልም ተስፋዬ ሸዋዬ (1981፡26) "ማንበብ አንድን መጽሃፍ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው መወጣት ወይም አንድን የቀረበ ጽሁፍ ከዳር እስከዳር ማንበልበል አይደለም፡፡" ብሏል፡፡ ከዚህ ብያኔ እንደምንረዳው ንባብ ማለት በወረቀት ላይ የሰፈረን ነገር ከዳር እስከዳር መሸምደድ ሳይሆን በጸሀፊውና በአንባቢው መካከል የሚደረግ የሥሜት ውህደት ነው ማለት ይቻላል፡፡ Teroka (112፡1998) ንባብን በሌላ መልኩ ሲያብራሩት ደግሞ

> "ንባብ ቃላትን ከመመልከት የዘለለ ንቃት የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ የንባብ ሂደት ጽሁፍን፣ አይን እና አእምሮን በአንድ ላይ ያካተተ ትርጉም የመፍጠር ሂደት ነው፡፡ በንባብ ጊዜ አእምሮአችን አስቀድሞ በምናውቀው፣ አሁን እየተማርነው ባለነው እና ለእኛ አዲስ በሆነ ነገር መካከል ትስስር ይፈጥራል፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡

ንባብ በምደሳሳው የመቀበያ ክሂል ቢሆንም ይህ በራሱ ድግም ውስብስብና የረቀቀ አዕምሮታዊ ተግባራትን ያቀፈ ነው፡፡ ‹‹ንባብ ግላዊ ነው›› ንባብ በጊዜ በቦታ ተከልሎ የሚገኝን የአንድ ፀሐፊን መልዕክት በመከተል ምላሽ ለመስጠት የምን ሞክርበት አዕምሮታዊ ተግባር ነው፡፡ ግላዊ ተግባር ስለሆነም የአነባቡን ሂደትና "ለፀሀፊውም የሚሰጠውን ምላሽ በቀጥታ ላናስተውል እንችላለን" Dievis (1995)

ስለ ንባብ ምንነት በርካታ ምሁራን የተለያዩ ሀሳቦችን ስንዝረዋል፡፡ እንደ John Attikins (1996፡38) "ንባብ ማለት መስተጋብራዊ ሂደት ነው፡፡" በማለት ይገልፃል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ንባብ ማለት በአንባቢያንና በፀሀፊው መካከል የሚደረግ የሃሳብ፣ ግንኙነት ሂደት ነው፡፡እንደ Williams (1984፡2) ደግም "ንባብ ማለት አንድን የተፃፈ ነገር አንብቦ የመገንዘብ ሂደት ነው፤፤" በማለት ይገልፀዋል፡፡

"ንባብ በአንድ ጽሁፍ አማካይነት ያሰፈረውን መልዕክት መረዳት እና ማገናዘብን ይመለከታል፡፡ እንዲህ ስለተባለ ግን መልእክቱ በጹሁፍ አማካይነት በቀላሉ ሰፍሮ የሚገኝ አለመሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ይኸውም የሰፈረውን መልእክት ለመረዳት ያንባቢን ንቁ አእምሮ እና ተሳትፎ ይጠይቃል" በማለት አለም (1997፡2) ይገልፃሉ፡፡

ስለ ንባብ ምንነት Anderson (1999) እንደገለጹት ንብብ ከተጻፈ ጹሁፍ ላይ መረጃ መውሰድ ብቻ ነው ብሎ መናገር ያስቸግራል፡፡ ይህውም አንድ አንባቢ የሚያነበው ለተለያዩ አላማ ነው ፡፡በመሆኑም ካላማው አንጻር የተለያዩ ውህድ ክሂሎችንና ስተራቴጂዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ስለዚህ ንብብ ለእውቀት ተብሎ ብቻ የሚነበብ ሳይሆን እንዳንባቢው አላማ ለተለያዩ ተግባራት የሚከወን በመሆኑ በውስጡ ሌሎች ንኡሳን ክሂሎችን አካቶ የያዘ ችሎታ ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ የአንብቢውን ብቃት የሚለካ ክሂል ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ Grellet (1981:8)"ንባብ ማለት መገመት፣ መተንበይ፣ ማመሳከር፣ እራስን ጥያቄ መጠየቅንና ንቁ ተሳትፎ ማድረግን የሚፈልግ ሂደት ነው፡፡በሂደቱም አንባቢ ክምንብቡ አውድ በመነሳት የአዳዲስ ቃላት ፊቺዎቸን የሚገመግምበት ገና ከመነሻው ባገኘው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የምንባቡን ዋና ይዘትና ወደፊት ምን እንደሚገጥመው የሚተነብይበት፣ ያነበበውን ጹሁፍ መረዳት አለመረዳቱን እራሱን የሚጠይቅበት፣በመጠየቅ የሚያመሳክርበት ሂደት መሁኑን እንረዳለን፡፡ በሌላ በኩል፤ የተለያዩ ምንባቦችን ሲያነብ የተለያዩ ችሎታዎችንና ስልቶችን መጠቀም እንዳለበት እንገነዘባለን፡፡

## 2.1.2. የንባብ ጠቀሜታ

ንባብ የሰው ልጅ በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ እድገቱን የሚያፈጥንበት፣ ሰብእናውን የሚቀርጽበት እና ማንነቱ ጠፍቶ እንዳይቀር ጠብቆ የሚያቆይበት ሂደት ነው፡፡ ማንበብ የማይችል ግለሰብ ነገሮችን የማወቅና የመግለጽ ብቃቱ በማየት እና በመስማት ላይ ብቻ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት የግለሰቡ የአመለካከት ብቃት አነስተኛ እና የተዛባ ይሆናል፡፡ Tieley(1973፡180) በዚህ ላይ አጽንኦት ሰጥተው ሲናገሩ "ማንበብ የማይችል ህጻን በአመዛኙ መጻፍም የማይችል ህጻን ይሆናል፡፡ ስለዚህም ማንኛውም የፈጠራም ሆነ የእውነታ ጽሁፍ ዕውቀቶች ከማያነብ ሰው የተሰወሩ ናቸው፡፡" ከዚህ ገለጻ የምንረዳው አለምን ለመረዳት ጽሁፍ እጅጉን ጠቃሚ መሳሪያ እንደሆነ እና የማያነብ ሰውም የሚያጣው ነገር ያለ መሆኑን ነው፡፡ በማህበረሰብ ደረጃም ካየነው የማንበብ ልምድ

የሌለው ማህበረሰብ ከእሱ በፊት ስለነበሩት ቀደምት ማንነቶቹ በተሟላ ሁኔታ የማያውቅ በመሆኑ "እኛ ማንነን?" የሚለው ጥያቄ ሁል ጊዜ እንዳስጨቀው ይኖል፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ የጽሁፍ ጥበብ እንዲዳብር የንባብ ልምድ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ "የጽሁፍ ጥበብ ማደግ ብቻውን ጥሩ ጸሃፊዎችን ባይፈጥርም እንኳን ንባብ ከፍተኛ የሆነ የቅድመ ሁኔታነት ድርሻን ይወጣል" በአንድ ማበረሰብ ውስጥ ጸሀፊዎች እንዲፈጠሩ አስቀድሞ የአንባቢዎችን መኖር ግድ ነው፡፡ (ባይርኒ 1991፡9) ፡፡

## 2.1.3. አንብቦ የመረዳት ምንነት

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምንነት ብዙ ምሁራን በየራሳቸው እይታ የአንብቦ መረዳት ትርጓሜዎችን ሰጥተዋል ። Panel (2000) አንብቦ የመረዳት በአንባቢው እና በፅሑፍ መካከል የሚደረግ ንቁ ሂደት መሆኑን 21 ያረጋግጣል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ እንደ Mayer(2003) አንብቦ መረዳት ተማሪዎች ትርጉምን ከጽሑፍ በማውጣት የተማሪዎችን ስኬታቸውን ለማሻሻል የሚያስችል ዘዴ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ እንደSnow(2002) ገለፃ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ትርጉምን በአንድ ጊዜ የማውጣት እና የመገንባት ሂደት ሲሆን እነሱም ሶስት ክፍሎችን አንባቢውን፣ ጽሑፉን እና የንባብ እንቅስቃሴን ወይም ዓላማን ያቀፈ ነው፡፡ Miller (2002) ገለፃ የአንብቦ መረዳትን ከማንኛውም የጽሑፍ ይዘት የመረዳት ወይም ትርጉም የማግኘት ችሎታ ነው፡፡ ከእነዚህ ትርጓሜዎች ጋር Millrood (2001) አንብቦ መረዳት የተጻፈውን ጽሑፍ በመረዳት፣መረጃን በማካሄድ እና አሁን ካለው ተሞክሮ ጋር በማዛመድ ትርጉምን ከጽሑፍ ለማውጣት የእይታ እና የእውቀት ሂደት ነው ሲል ያረጋግጣል።

## 2.1.4. የአንብቦ መረዳት ክሂልን ማዳበር

የሰዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር አለመዳበር ለማወቅ ወይም ደግሞ በሌላ መንገድ አንብበው መረዳታቸውን መግለፅእንዲቻል ብዙ ግብአቶች ሊደረግላቸው እንደሚገባ ይታመናል፡፡ ከነዚህም ግብአቶች አንደኛው ለተማሪዎች ከተለያዩ የንባብና የአንባብ ስልቶች ጋር ማስተዋወቅና በሚገባ ማላመድ ነው፡፡ ምክንያቱም የብዙ ጊዜ ልምምድ ውጤታማ እንደሚያደርግ የህይወት ተሞክሮ ያሳያልና ተማሪዎችም ለዚህ አይነቱ ልምምድ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል፡፡

የንባብ ንዑሳን ክሂሎች መዳበር ብሎም መጎልበት እንዲችሉ ተማሪዎች ከተለያዩ የንባ ስልቶች ጋር መተዋወቅና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ማለማመድ ወሳኝነት ያላቸው

ናቸው፡፡ ሲሉ Grilit (1981) ይገልፃሉ፡፡ ስለሆነም ከዚህ መረዳት የምንችለው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በብዛትና በበቂ ሁኔታ መለማመድ የአንብቦ መረዳት ብቃት ማዳበርን ያረጋግጣል ማለት ነው፡፡

### 2.1.5. የንባብ ንዑሳን ክሂሎች

ንባብ የተለያዩ ንዑሳን ክሂሎችን በውስጡ የሚይዝ ሰፊና መሠረታዊ ክሂል ነው፡፡ ከእነዚህ የንባብ ንዑሳን ክሂሎች መካከል ጥቂቶቹን ለማለት ያህል

ድምጾችን /ፊደሎችን/ አገጣጥሞ ቃላትን መጥራት፣ቃላትን አገጣጥሞ ሀረጋትን ፣ ሀረጋትን አገጣጥሞ ዐ/ነገር መጥራት/ማንበብ፣በግልፅ የሰፈረን ወይም የታተመን መረጃ አንብቦ መረዳት፣ጽንሰ ሃሳባዊ ትርጉምን መገንዘብ መረዳት፣በዐረፍተ ነገሮች መካከል የሚኖረውን ዝምድና መለየትና መረዳት፣ዋና ሃሳብና ደጋፊ ሃሳቦችን መለየት፣ጠቃሚ የሆኑና ጠቃሚ ያልሆኑትን ነጥቦች እያነገዋለሉ ለይቶ ማውጣት ፣የምንባቡን ዋና ሃሳብ ጨምቆ ማቅረብ እንዲቻል ዋና ዋና ነጥቦችን መለየት የሚሉት ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ስለዚህ እነዚህን የንባብ ንዑሳን ክሂሎችን ተማሪዎች በአግባቡ ማዳበር እንዲችሉ የሚዘጋጀት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በሌሉበት ሁኔታ ወይም ቦታ ውስጥ ንባብን ለማስተማር መሞከር የሚጠበቀውን ውጤት አያስገኝም፡፡ አስቀድሞ እንደተገለፀውም ለንዑሳን ክሂሎች መዳበር አነስተኛ የማይባሉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሊሰናዱ ይገባል፡፡

የንባብ ንዑሳን ክሂሎችን ለማዳበር የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመልመጃ መልክ ማዘጋጀትአስፈላጊ እንደሆነ ተደጋግሞ የተወሳ ነው፡፡ ሆኖም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በሁለት መልክ ቢዘጋጁ ይበልጥ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ እነርሱም፡-

የምንባቡን ጠቅላላ የአቀነባበር ወይም የአደረጃጀትን መንገድ እንዲገልፁ የሚያስችሉ ጥያቄዎችንና መልመጃዎችን ማሰናዳት፡፡ የምንባቡን ይዘት እንዲያብራሩና እንዲገለፁ ማድረግ ወይም በዚህ ዙሪያ የመለማመጃ ጥያቄዎችን ማቅረብ ናቸው፡፡

ይህን ጉዳይ ዘርዘር ባለመልኩ ለመመልከት ስንሞክር በምንባብ ላይ የተመሰረቱ የአብቦ መረዳት ጥያቄዎች የምንባቡን ጠቅላላ የአቀነባበር ወይም የአደረጃጀት ሂደት ተማሪዎች በራሳቸው እንዲገልፁ ማድረግ በዚህ ስር ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

የምንባቡን ተግባር መጠየቅ/መዘርዝራዊ ቀስቃሽ ወይም ኮነታዊ/፣የምንባቡን አይነት መጠየቅ፣በምንባቡ ውስጥ ስለአያያዥ ቃላት ተግባር መጠየቅ ፣በዐረፍተ ነገሮች መካከል ሲላለው ዝምድና መጠየቅ በሁለተኛው ስር በውስጠታዋቂነት የተገለፁ ጉዳዮችን በምንባቡ መሰረትነት እንዲያብራሩ፣በግምት ወይም በይመስላል ሊደረስባቸው የሚችሉትን ልዩ ልዩ ትርጉሞችን፣በምንባቡ የቀረበውን ሃሳብ እንዲገመግሙ ወይም እንዲመዝኑ መጠየቅ

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን መንገዶች ተከትለው የምንባቡን ተግባርና ይዘት መሰረት በሚያደርግ መንገድ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ተማሪዎችን ከተለያየ የአነባበብ ስልት ጋር ያስተዋውቃል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታንም ከፍ ያደርጋል፡፡ ለዚህም ነው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ሂደት ውስጥ የእያንዳንዱ ጥያቄ ዓላማ ቅርፅና ዓይነት ሊተኮርበት ይገባል፡፡ የሚባለው፡፡ ይህም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ዝግጅት የምንባቡን ተግባርና ይዘት ብቻ በመመርኮዝ ሳይሆን በአደረጃጀትም ረገድ ትልቅ ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባም ያመለክታል፡፡

## 2.1.6. የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፈተናዎች

- አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና በሚዘጋጅበት/በሚፃፍበት ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ማስገባት እንዳለብን Hughes(1989) እና Madsen (1983:83-84) ይገልፃሉ፡፡
    - ጥያቄዎች ተማሪዎቹ የምንባቡን ሃሳብ ሳይረዱ ወይም ምንባቡን ሳያነቡ የሚመልሱዋቸው መሆን የለባቸውም፡፡
    - የጥያቄዎቹ መልሶችም በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ወይም በምንባቡ መሠረት የሚመልሱ ሊሆኑ ይገባል፡፡
    - አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የምንጠቀማቸው ምዘናዎች ከተወሰነ ባህል ጋር የተሳሰሩ መሆን የለባቸውም፡፡
    - እንዲሁም ጥያቄዎቹ ከምንባቡ እንዳለ ቃል በቃል ተወሰደው የሚቀረቡ መሆን የለባቸውም ነገር ግን በቀላልና ግልፅ ቋንቋ መፃፍ አለባቸው፡፡
    - የአንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የምናዘጋጀው ፈተና ከቋንቋ ክሂል ውጭ በሆነ ዕውቀት የሚመለሱ መሆን አይኖርባቸውም ይላሉ፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሁሉንም የምንባቡን ክፍሎች የሚዳስሱ፣ ከምንባቡ መጠን አኳያ በቂ ቁጥር ያላቸው፣ በአይነት የተለያዩና ልዩ ልዩ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለካት የሚረዱ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ሂደት የሚደግፉ የቋንቋ ችሎታ ደረጃቸውን ያገናዘቡ እንዲሆኑ Nuttal (2000፡190) ይመክራሉ፡፡ እስካሁን ከቀረቡት የምሁራን አስተያየቶች የምንረዳው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች ሲዘጋጁ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ መሆናቸውን ነው፡፡

Nuttal (1982፡37) አንድ አንባቢ የአነበበውን ጽሁፍ ካልተረዳ ምንበቡ ዋጋ የለውም፡፡ ስለዚህ መረዳቱ መታወቅና መወሰን አለበት፡፡ ይህ ሁኔታ እንደ ዓላማ ለመውሰድ ምርጫ ፣ እውነት(ሀሰት) ጥያቄዎችን በመጠቀም መለካትና ማረጋገጥ ይችላል፡፡ ግን የትኛው ውጤት እንደ ጥሩ መረዳት ይወሰድ በአጠቃላይ አመለካከት ሲታይ 70% መረዳት ይበቃል፡፡ የትኛውስ የተሻለ አንባቢ ነው? 100% ውጤት አግኝቶ በደቂቃ 140 ቃላት ያነበበ ወይስ 70% ውጤት አግኝቶ በደቂቃ 200 ቃላት ያነበበው? የትኛው ውጤት አጥጋቢ ነው? ወይም የትኛው ጥሩ አንባቢ ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች ቁርጥ ያለ መልስ አላገኙም፡፡ ነገር ግን 70% አንብቦ የመረዳት ችሎታ በቂ ነው የሚል አይታ እንዳላቸው Nuttal (2000፡50) ይገልፃሉ፡፡ ከላይ የቀረበውን የምሁራን አስተያየት ከግምት በማስገባት በዚህ መሰረት አጥኝው አካሄዱን በዋናው የጥናት ስራው ላይ የሚተገብረው ይሆናል፡፡

Anderson(1999፡3) እንደገለፁት የማንበብ ፍጥነትን አስመልክቶ የሚወጡ መረጃዎች እርስ በእርሳቸው የሚጋጩበት ሁኔታ አለ፡፡ አንዳንድ ፀሀፊዎች በብቃት አንብቦ ለመረዳት ከተፈለገ በደቂቃ 180 ቃላትን ማንበብ መቻል እንደ ዝቅተኛ የማንበብ ፍጥነት ሊወሰድ ይችላል ይላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በደቂቃ 200 ቃላትን ከመቶ በመቶ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ማንበብ እጅግ አነስተኛ ፍጥነት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም አንዳንዶቹ ምሁራን በደቂቃ 300 ቃላትን ማንበብ መቻል በቂ የምንበብ ፍጥነት ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

ከነዚህ ምሁራን ሃሳብ የምንረዳው በቂ የማንበብ ፍጥነትን በተመለከተ ቁርጥ ያለ ብያኔ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ነው፡፡ በዚህም አጥኝው በተከታይ በሚያደርገው ጥናት ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥረት እንደሚጠበቅበት ያመለክታል፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የሚዘጋጁ ምንባቦች ለአንባቢዎቹ የሚስማሙ እንደሆኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሲባል የምንባቡ የክብደት ደረጃው፣ ውስብስብነቱ፣ ባህላዊ ገፅታው ፣ የቀረበበት ርዕስና መጠኑ የተማሪዎችን ደረጃ ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ በማለት Heaton(1975፡12) ይገልፃሉ፡፡ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ወቅት የፈተናዎቹ አስተማማኝነት እና ትክክለኛነት ታሳቢ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ Heaton (1991፡159) ትክክለኛነት ፈተናውን በመፈተን የተፈለገውን ችሎታ ወይም ክሂል በትክክል መለካት መቻሉን የሚመለከት ፅንስ ሃሳብ ሲሆን አስተማማኝነት ደግሞ አንድ ፈተና ተደጋግሞ ቢሰጥ የሚያስገኘው ውጤት ምን ያህል እንደሚቀራረብ የሚያመለክት ነው፡፡ በማለት(Hughes 1989:3) ይገልፃሉ፡፡

## 2.1.7 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን መስፈርቶች አስቀምጠዋል፡፡ ከነዚህ ምሁራን መካከል አንዱ የሆኑት Hughes (1989፡119) እንደሚገልፁት በመሰረቱ አንድ ፅሑፍ የያዘውን ሃሳብ ወይም መልዕክት ተፈታኞች ሙሉ በሙሉ ተረድተውታል ለማለት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በሙሉ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገር ግን የሰው አዕምሮ በጽሁፍ የቀረቡ ሃሳቦችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት የሚገነዘብ በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ተፈታኞች ከ80 በመቶ በላይ ውጤት ካስመዘገቡ የቀረበውን ጽሁፍ ተረድተውታል ማለት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም ለማንበብ ፍጥነቱም ሆነ ያንብቦ መረዳት ችሎታ የተለያዩ አንባቢዎች በተለያየ ፍጥነትና የመረዳት ችሎታ ደረጃ የሚያነቡ ስለሆነና እሳቢዎቹም በአንጻራዊነት የሚገለጹ ስለሆነ የደረጃ መስፈርቱ ከፍ ሲል በተገለጸው መሰረት ቢቀመጥ የተሻለ እንደሚሆን ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡Madsen(1983:91)እና ሌሎች፣ ተማሪዎች ከበቂ ፍጥነት ጋር የተሰጣቸው ችሎታ መግቢያ ፈተና ያመጡት ውጤት ከ40በመቶ በታች ከሆነ በጣም ዝቅተኛ፣ ከ50-41 በመቶ ዝቅተኛ ፣ከ69 -51 በመቶ መካከለኛ ፣ከ70-80 በመቶ በቂ፣ ከ81 በመቶና ከዚያ በላይ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው በማለት ማስቀመጥ ይቻላል፡ ፡ምክንያቱም አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማናበብ ፍጥነት እንደ አንብቢዎቹ የሚለያዩ ስለሆነ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

Narayanswamy (1975-144-147) ደግሞ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤቱን ሲገልጹ ከ10 ከታረመ ፈተና ከ9-10 ውጤት ያስመዘገቡ ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ፣ ከ7-8 ያስመዘገቡ በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው ከ5-6ያስመዘገቡ ዝቅተኛና ከ5 በታች ያስመዘገቡ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የሆነ የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተብሎ እንደሚፈረጁ ይግልጸሉ፡፡ ባጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ መስፈርት የተፈታችን የችሎታ ደረጃ ለመመዘን የተሸለ እንደሚሆን ምሁራን ይገልፃሉ በተለይ አማካይ ችሎታ ላላቸው ተፈታኞች በተመለከተ የመቀራረቡ ሁኔታ መኖሩን መገንዘብ ያቻላል፡፡

## 2.1.8 የንባብ ፍጥነት ምንነት

እንደ Nuttal (1982፡36) ገለፃ የንባብ ፍጥነት ማለት እንድ አንባቢ ከተፃፈ ፅሑፍ ላይ ምን ያህል ቃላት በደቂቃ ያነባል ማለት ሲሆን የንባብ ፍጥነት የሚለካው በደቂቃ ውስጥ በምናነበው የቃላት ብዛት ይሆናል፡፡ የንባብ ፍጥነት ሲሰላ የሚከተለውን ፡ቀመር መሠረት ያደርጋል፡፡

እንደምናነበው ነገር ወይም ይዘት የምናነበው የቃል ቁጥር በደቂቃ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡ ይህንን አስመልክተው nuttal{1992} የሚከተለውን ይገልጻሉ፡፡ የንባብ ፍጥነታችን እንደምናነበው ይለያያል፡፡ይኸውም ከአስሳ ንባብ እስከ ጥልቅ ንባብ ያሉ የንባብ ቲክኒኮችን የሚፈልግ ሊሆን ይችላል፡፡ የመዝናኛ ንባብና የጥናት ንባብ ይለያያል፡ ፡ይህንን ማወቅ ለፍጥነት ንባብ አጠቃቀም እንደመስረታዊ ጉዳይነው፡፡በመሆኑም የንባብ ፍጥነት ክህሎት ማዳበር ብቻ መረዳትን ያመጣል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም በንባብ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቴክኒኮች (ይዘቶች) ግን ተጸእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ይሁን እንጂ ለአንብቦ መረዳት ያለው አስተዋጸኦግን ቸል የሚባል ጉዳይ አይሆንም፡፡

Anderson (1999, 104) የንባብ ፍጥነት ክህሎትን ማዳበር ለተማሪዎች እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ በክፍል ውስጥ ግን የተተወ ወይም የተረሳ ክሂል ነው…” ብሏል ይህን ሀሳብ Grabes stoller (2007,19) በሚከተለው መንገድ ገልፀውታል፡፡ አንድ የሚነበብ የቤትስራ ለተማሪዎች እንሰ ጣቸዋለን ይህን ስራ ከሰጠናቸው በኃላ ስራውን ለማንበብ ምን ያህል ጊዜ እንደፈጀባቸውና በምን መንገድ እንደተረዱት አንጠይቃቸውም አንዱ ተማሪ በ30 ደቂቃ አንብቦ ሰርቶት ይሆናል፣ ሌላው ደግሞ አንድ ለሊት ወስዶበት ይሆናል፣ ይህም ሆኖ

ምንባቡን ላይረዳ ይችላል፡፡ ይህን ከግንዛቤ አስገብተን ማለትም በምን ያህል ጊዜ (ፍጥነት) እንዳነበቡትና እንደተረዱት በአግባቡ አውቀን ተማሪዎቻችንን አናርማቸውም ወይም በማለማመድ አናስተካክላቸውም በመሆኑም በንባብ ፍጥነት ደካማ የሆኑ ተማሪዎች እንዲሁ ባሉበት ሁኔታ ይቀራሉ ብለዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነትና የመረዳት አቅማቸውን ተገንዝቦ እገዛ ማድረጉ ትኩረት ያልተሰጠው እንደሆነ ነው፡፡

ሌላው እንደምናነበው ነገር ወይም ይዘት የምናነበው የቃል ቁጥር በደቂቃ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል ይህን አስመልክተው Nuttal (1982፡47) የሚከተለውን ይገልፃሉ የንባብ ፍጥነታችን እንደምናነበው ጉዳይ ይለያያል፡፡ ይኸውም ከአሰሳ እስከ ጥልቅ ንባብ ድረስ ያሉ የንባብ ስልቶችን የሚፈልግ ሊሆን ይችላል፡፡ የመዝናኛ ንባብና የጥናት ንባብ ፍጥነት ይለያያል፡፡ ይህን ማወቅ ለፍጥነት ንባብ አጠቃቀም አንዱ መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የንባብ ፍጥነት ክሂሎች ማዳበር ብቻ መረዳትን ያመጣል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም በንባብ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቴክኒኮች(ይዘቶች) በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በአንብቦ መረዳት ላይ እና በፍጥነት ንባብ ላይ የራሳቸው ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡

ይሁን እንጂ ለአንብቦ መረዳት ያለው አስተዋጽኦ ግን ቸል የሚባል አይደለም፡፡ የተለያዩ ቋንቋ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ በረታታሉ፡፡ በተገቢው የንባብ ሂደት ውስጥ እንዲገደቡና እንዲያነቡ ይሰለጥናሉ በማለት Anderson(1999፣112) ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች ከሚያነቡት ዓላማ አኳያ የፅሑፍ አይነት አንፃር ስልታቸውን በመለዋወጥ የማንበብ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ መርጋት ተገቢ ነው፡፡

### 2.1.9 የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ

የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ እንደለው ምሁራን ያስገነዝባሉ ከነዚህም ውስጥ Nuttal s(1982፡33) ጥሩ አንባቢ ቃል በቃል አያነብም፡፡ ከደካማ አንባቢ በተሻለ ፈጣን የአይን እንቅስቃሴ ሲኖረው በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ቃላት በመቃኘት ቃል በቃል ሳይሆን በአፍታ እይታ ማንበብ መቻል ነው ፈጣን አንባብያን በአንድ በተፃፈ ነገር ላይ ያለውን ቃል እየቆጠሩ ሳይሆን እያይዘውና አከታትለው ስለሚያነቡ የሀሳብ መቆራረጥ ወይም መበጣጠስ ችግር አያጋጥማቸውም

ይህም የተሟላና ትርጉም ያለው ሃሳብ ለመያዝ ያግዛቸዋል በመሆኑም የመረዳት አቅማቸው ከፍተኛ ነው በሌላ መልኩ አዝጋሚ አንባብያን የመረዳት አቅማቸው ደካማ ነው፡፡ ምክንያቱም ሀሳቡን ቆራርጠው ስለሚያነቡ የዐረፍተ ነገሩንም ሆነ የአንቀጹን ሃሳብ ተያያዥ በሆነ መልኩ አያገኙትም፡፡ በዚህም መጨረሻ ላይ ሲደርሱ የመጀመሪያው ምን እንደሆነ መረዳት አይችሉም አንባቢው አንብቦ ከጨረሰ በኃላ የሚያስበው ስላነበባቸው ተናጠል ቃላት እንጂ ስለ አጠቃላይ ጽሁፍ አይደለም በዚህም የመረዳት ችግር ያጋጥመዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ የመረዳት ጋር የተሳሰሩ መሆኑን ነው፡፡

Anderson (1999፡2) ይህን የNuttal ሃሳብ አጠናከረው ሲገልፁት በቂ የሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታማለት ያነበቡትን ጽሁፍ ወይም ምንባብ በብቃት መረዳትና ማስተወስ ብቻ ሳይሆን በታቻለ መጠን በጥሩ ፍጥነት አንብቦ መረዳትንም የሚያጠቃልል መሆኑንና አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነትም ጎንለጎን ሊዳብሩ እንደሚገባ ገልፀው ከዚሁ ጋር በማያያዝ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸውን አሳድገው ጥሩ አንባቢ ሊሆኑ የሚችሉት የንባብ ፍጥነታቸውንብቻ ሳይሆን አንብበው የመረዳት ችሎታቸው አድጎ ጥሩ ደረጃ ላይ ሲደረስ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

የተለያዩ ምሁራን በንባብፍጥነትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ጥብቅ ቁርኝት እንዳለ ገልፀዋል፡፡እንዲሁም የፍጥነት ንብብና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ቁርኝትም ውስብብስ ነው፡፡ከዚህም የተነሳ ሁለቱም ንኡሳን ክህሎች በአንድነት መዳበር እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

Perfetti (1985፡12)ይህን ሀሳብ ሲገልፁ የንባብ ችሎታ ብያኔ የሚመነጨው ከንባብ ፍጥነትና ከአንብቦ መረዳት ግንዛቤ ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ጥሩ የንባብ ችሎታ ያለው ሰው በአማካይ ከሚታወቀው የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ደረጃ በላይ አንብቦ መረዳትና በፍጥነት ማንበብ ይጠበቅበታል፡፡ ይህም የንባብ ችሎታ መለኪያ ዕድሜንና የትምህርት ደረጃን መሠረት ያደረገ ይሆናል" በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳው የንባብ ችሎታ ማለት ከንባብ ፍጥነትና አንብቦ ከመረዳት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ ይህንኑ ሀሳብ Perfetti (1985፡10) ሲያጠቃልሉ "መሠረታዊ የሆኑት የማንበብ ችሎታ መለኪያዎች ጥሩ የንባብ ፍጥነትና የመረዳት አቅም ናቸው" ብለዋል፡፡ ስለዚህ የንባብ ፍጥነት ደረጃችንና አንብቦ የመረዳት አቅማችን በየጊዜው ማሻሻል ይገባል ይላሉ፡፡ ይህን

አስመልክተው Bell (2001,101) በጥናት እንዳመለከቱት በፍጥነት የሚያነቡ ሰዎች ወሳኝ በሆነ መልኩ ከፍተኛ የመረዳት ችሎታ አላቸው በማለት ገልፀው በዚህ መልክ አብራርተዋል፡፡

ከፍተኛ የንባብ ችሎታ ያላቸው አናንባቢዎች 1000 ቃላት በደቂቃ ሲያነቡ የመረዳት ችሎታቸው ደግሞ 85% እንደሆነ በመጥቀስ እነዚህም  በአጠቃላይ አንባቢዎች 1% የሚሆኑ መሆናቸውን ያሳያሉ አያይዘውም አብዛኞዎቹ አንብቢዎች 200 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ሲሆን የመረዳት ችሎታቸው 60% እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት መካከለኛ አንባቢዎች ከፈጣን አንባቢዎች አምስት ጊዜ እጥፍ ያዘግማሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡ ከንባብ ንዑሳን ክሂሎች ውስጥ አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ  ነው፡፡ የፍጥነት ንባብም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ አንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት በአንድነት መዳበር ያለባቸው ክሂሎች እንደሆኑ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ በፍጥነት ማንበብ ነገሮችን በቀለጠፈ መልኩ ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ዘገምተኛ አንባቢዎች አንድን ጽሁፍ አንብበው የመረዳት ችሎታቸውን ዝቅተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም አንብቡ፣ መረዳት ከንባብ ፍጥነት ክሂል ጋር ዝምድና እንዳለው አንዱ መኖር ለአንዱ ህልውና ወሳንነት እንዳለው ይገልፃሉ:: Nutall 1982,33) በሌላ በኩል Anderson ( 1999) ዝቅተኛ የንባብ ልምድ ያላቸው ፊደል በመቁጠር የሚያነቡ በደቂቃ 1 100 ቃላት ሲያነቡ የመረዳት አቅማቸው ከግማሽ በታች ነው፡፡ ዕድሜያቸው ከ6-12 የሆኑ ተማሪዎች ከ100-200 ቃላት በደቂቃ ማንበብና 50% የመረዳት አቅም እንዲኖራቸው ይፈለጋል፡፡ በአብዛኛው አንባቢ ደግሞ ከ200-250 ቃላት በደቂቃ ማንበብና ከ50% በላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ይጠበቅበታል፡፡ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸው በማጠናቀቅ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ከ250-350 ቃላት በደቂቃ ማንበብ ሲኖርባቸው የመረዳት አቅማቸውም ከግማሽ በላይ መሆን አለበት፡፡ የተሻለ የማንበብ ደረጃ ላይ የሚገኙና ጥሩ የመረዳት አቅምና ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች ከ350-500 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ሲሆን 75% አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው፡፡ በጣም ውጤታማ የሆኑ አንባቢዎች ከ800-1000 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ሲሆኑ ከ75% በላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው እንደሆኑ ይገልፃሉ… በአጠቃላይ ከዚህ የምረዳው 1000 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ሰዎች እጅግ በጣም ጥሩ አንባቢዎች የመረዳት አቅማቸውም ከፍተኛ እንደሆነና ከ1-100 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ደግሞ ዝግተኛ

አንባቢዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ የመረዳት አቅማቸውም ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

Nuttal (2000-54)እና Anderson(1992:2) አንባቢዎች የንብብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር በሚያደርጉት ጥረት የንባብ ፍጥነታቸውን በማሻሻል ብዙ አንባቢ ሊሆኑ እንደሚችሉና በፍጥነት ንባብና በአንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ትስስር እንዳለ ይገልጻሉ፡፡

## 2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኝዋ ይህንን ጥናት ለማዘጋጀት የተለያዩ ልምድና ስልቶችን ለማወቅ ከራስ የጥናት ርዕስ ጋር ተመሳሳይነት ያለቸውን በተለያዩ ጊዜያት የተሰሩ ቀደምት ጥናታዊ ጽሁፎችን ማየትና መፈተሽ የግድ መሆኑን በመረዳት በርካታ ጥናታዊ ጽሁፎችን ለመቃኘት ሞክራለች፡፡ በዚሁ መሠረት የአጥኝዋ የትኩረት አቅጣጫ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ላይ ሲሆን ለጥናታዊ ምርምር ስራው እንዲረዳት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች በዚህ መልክ ቃኝታለች፡፡

በረከት ሁሴን (2010) በሰገን አከባቢ ሕዝቦች በሰገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በአማርኛ ቋንቋ ኢ. አፍ ፊት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በመፈተሽ ማጥናት ነው፡፡
ጥናቱም በመረጃ ሰብሳቢነት ፈተና እና ቃለ መጠየቅን የተጠቀመ በመሆኑም ከዚህ ጥና ጋር ሲመሳሰል የጥናቱን ተተኳሪ ተማሪዎች እና የትምህርት ቤት አመራረጥ ለመምረጥ የተጠቀመበት የንሞና ዘዴ አላማ ተኮር የንሙና ዘዴ በመሆኑ ከዚህ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም በጥናቱ ላይ ያሳተፋቸው ተማሪዎች ከ4 የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ተመርጠው የቀረቡ በመሆናቸው በተማሪዎቹ አመራረጥ ከዚህ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በሚል ርዕስ መሰራቱ ተመሳሳይ ያደርገዋል፡፡ የተገኘው የጥናት ውጤትም የተማሪዎች አንበቦ የመረዳት ችሎታ እና የንብብ ፍጥነት ተዛምዶ ዝቅተኛ መሆኑን አመላክቷል፡፡
ተሾመ (1997) በከምባታ ጠምባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችና የማንበብ ፍጥነታቸው በሚል ርዕስ ያጠኑት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት

ቢኖረውም ከክፍል ደረጃ ከቦታና ከዘመን ልዩነት በተጨማሪ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ኢ-አፈፊት በሆኑ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ ከተሾመ ጥናት የተለየ ያደረገዋል፡፡

አያሌው (2001) በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአንብቦ የመረዳት ክሂል ጋር ያለው ተዛምዶ በወልዲያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተመሰረተ ጥናት በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ቋንቋው በአፍ መፍቻነትና በትምህርት መስጫነት በስፋት በሚያገለግል ክልል ውስጥ የተካሄደ በመሆኑና በመሰናዶ ተማሪዎች ላይ የተደረገ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት ያለው ሆኖ እናገኛለን፡፡ ምክንያቱም ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በ10ኛ ክፍል ኢ-አፈፊት ተማሪዎች ላይ በመሆኑ ነው፡፡

መኮንን (2000) የቀደመ ጥናት ጋር በከፊል በሚገናዘብ ውጤት የቀረበ ነው፡፡መኮንን (2000) በአዊኛአፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ግምገማ በሚል ርእስ ያቀረበው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው አንብቦየመረዳት ችሎታን መገምገሙ እና በሁለተኛ ቋንቋተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ሲሆን እንዲሁም እንዲሁም ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መኖሩን አመላክቷል፡፡ነገር ግን ምንም እንኳን በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ቢያተኩርም፣ የማንበብ ፍጥነትንከአንብቦ መርዳት ጋር ያለውን ተዛምዶ አልቃኘም፡፡በመሆኑም የንባብ ፍጥነትን ከአንብቦ ምረዳት ነጥሎ መገምገሙ ከዚህ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህን ጥናት ከግብ ለማድርስ የተመረጠው ተዛምዷዊ (Correlation) የምርምር ስልት ነው፡፡ ለዚህም ወካይ የሆኑ በሸክኛ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በእድል ሰጪ የእጣ ናሙና ተመርጠው ጥናቱ ተከናውኑዋል ፡፡ በዚህ ጥናትበመመርኮዝ የተጠኝዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታናየንባብ ፍጥንት ተዛምዶ መርምሮ ለማቅረብ ተችሏል፡፡ ጥናቱም በመጠናዊና ገላጭ የምርምር ዘዲ ተተንትኗል፡፡

### 3.2 ተጠኚዎችና የናሙና አውሳሰድ

#### 3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ስር ከሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የኩቢጦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና ተመርጧል፡፡

ምክያንቱም ጥናቱን ለማካሄድ ይበልጥ አመቺ በመሆኑና አጥኝዋ በዚሁ ትምህርት ቤት ለ6 ዓመታት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በማስተማር ላይ የቆየችና በሚጠናው ጥናታዊ ርዕስ ዙሪያ ቀድሞ የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ /የምርምር ስራ/ ማግኘትአለመቻሏ የትኩረት አቅጣጫ ሊሆን ችሏል፡፡ የኩቢጦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስሩ ተቀብሎ የሚያስተምራቸው ተማሪዎች ከተላያዩ የቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦች የተወጣጡ ቢሆኑም አብዛኛውን ተማሪዎች ውልደታቸው በከተማ ውስጥ ስለሆነ የአማርኛ ቋንቋ ከሌላው የቋንቋ ተናጋሪ ባላነሰ ደረጃ የሚጠቀሙ በመሆናቸው ጥናቱን የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሸክኛ በሆኑት ላይ ማተኮር አመቺ ሆኖ በመገኘቱና በተጨማሪም የምታስስተምርበት ትምህርት ቤት በመሆኑ ወጪ ጉልበትና ጊዜን ይቆጥባል ተብሎ ስለሚታመን አጥኝዋ በትምህርት ቤቱ ላይ አተኩራለች፡፡

#### 3.2.2 የክፍል ደረጃና የተማሪዎች አመራርጥ

ዘጠንኛ ክፍል ለጥናቱ ተስማሚ በመሆኑ በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ ምክንያቱም አጥኝዋ በጥናቱ በተመረጠው ክፍል ተከታታይ ለሆኑ 6 አመታት በማስተማር ላይ የቆየች በመሆኑ ይበልጥ በዚህ ክፍል ተማሪዎች ለይ ጥናቱን ማካሄድ ተመራጭ ሆኗል፡፡

### 3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራርጥ

በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ኩቢጦ ከተማ ኩቢጦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2016 ዓ.ም በ5 የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተመድበው በመማር ላይ ያሉ 420 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ከነዚህ መካከል በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፊት ከሆኑ ተማሪዎች ውሰጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሸክኛ ቋንቋ የሆነውን የጥናቱ ተተኳሪ ሆነው በተመርጠዋል፡፡ ከ420 ተማሪዎች ውስጥ 100 ተማሪዎችን እድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም በየክፍሉ ለጥናቱ ታታሪ የሚሆኑ 20 ተማሪዎችን  ዕድል በመስጠት በጥቅሉ 100 ተማሪዎችን ተተኳሪ በማድረግ አጥኚዋ ጥናቱን አካሂዳለች፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ጥናቱ የሚያተኩረው በሸክኛ አፍ ፊት ተማሪዎች ላይ ስለሆነ የሌላ ቋንቋ አፍ ፊቶችን ከሸክኛ አፍፊት ለመለየት ሲባል ነው፡፡

### 3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብዛት ወንድ ሁለት ሴት ሁለት በድምሩ አራት ሲሆኑ፣ ከነዚህ አራቱ መካከል አንዷ ጥናቱን የምታካሂደው መምህርት ሰትሆን ቀሪዎቹ ሶሰት መምህራን ቁጥራቸው አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሦስቱም የጥናቱ አካላይ ወይም ተተኳሪዎች ሆነዋል፡፡

መምህራኑን መምረጥ ያስፈለገበት ምክንያት ለጥናቱ ተተኳሪዎች የሚቀርቡ የአንብቦ መረዳት ፈተና እና የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተናዎችን በተገቢው ሁኔታ መስጠት እንዲቻልና የተገኘውንም ውጤት ለማጠናቀር በጋራ መስራቱ ጠቀሜታ ስላለዉ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ለሚሰጡት ፈተናዎች ተገቢ ቁጥጥር ማድረጉ አስፈላጊ ስለሚሆን እና በአጥኝዋ ብቻ ሊከወን ሰለማይችል ነው፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በዋናነት የሚያገለግሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችም ፈተና እና ለመምህራን የቀረቡ ቃለ መጠይቆች ናቸው ፡፡

### 3.3.1 ፈተና

ለጥናቱ የተመረጠው ዋና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ፈተና ነው ፡፡ለዚህም ሁለት አይነት ተራ በተራ የሚሰጡ ፈተናዎች ተዘጋጅተዋል፤ እነዚህም ፈተናዎች የንባብ ፍጥነትና

የአንብቦ መረዳት ችሎታን የሚለኩ ናቸዉ፡፡ ሁለቱም ፈተናዎች በጥናቱ ሲካተቱ ለተማሪዎች ከመቅረባቸውም በፊት በትምህርት ቤቱ በሚገኙ ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህርራን እንዲሁም በአማካሪዬ አስተያት ተሰጠባቸዋል፡፡ ከተገኘውም ግብረ መልስ በኋላ በተገቢ ሁኔታ ተስተካክለው ሁለቱም ፈተናዎች የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነትና ፤ አንበቦ የመረዳት ችሎታ እንዲመዝኑ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡ ሁለት ምንባቦች ተመርጠዉ የጥናቱ ተተኳሪዎች የንባብ ፍጥነታቸውን የሚለካ ሲሆን በጣምራነት የተጠኝዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ከየምንባቡ አስር አስር ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ያለበትን ደረጃ ለማወቅ እንዲረዳ የሚያስችሉ ፈተናዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

## 3.3.2 ቃለ መጠይቅ

ለጥናቱ በአጋዥነት የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ ነው። ያለው እንዳወቀ (1998) ቃለ መጠይቅ በአንድ ጉዳይ ዙሪያ ጥልቅ የሆነ ስፋት ያለውና የተብራራ ምላሽ ለማግኘት ከማስቻሉም በላይ የተሰጠውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በምላሹ በጽሁፍ ያልተገለፁ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስችል ዜዴ ነው፡፡ በመሆኑም በፈተና አማካይነት የተገኘውን መረጃ ለማጎልበት ይረዳ ዘንድ ከጥናቱ ተተኳሪዎች ውጭ ሁለት 10ኛ ክፍል አማርኛ ለሚያስተምሩ ወንድ መምህራንና 1 የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ለምታስተምር መምህርት በመጠኑ የተደራጀ ቃለ መጠይቅ ቀርቦ ከመምህራኑ የተገኙው ምጋቤ ምላሽ መረጃ ተሰብስቦና ወደ ጽሁፍ ተገልብጦ የጽሁፍ ትንተና ተሰጥቶበታል፡፡

በቃለ መጠይቁ የመምህራኑ አጠቃላይ ዳራ፣ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርትን የሚያቀርቡበት ዘዴና ስለተማሪዎቻቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ያላቸውን አስተያየት እንዲሁም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት የሚገጥማቸውን ችግርና የመፍትሔ ሀሳቦችን የሚያመላክቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኩቢጠ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኑ በሸክኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሸ ነው፡፤ ስለሆነም በአንብቦ መረዳት ችሎታና በንባብ ፍጥነት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለማሳየት በ (Persont product Mesurment Correlation) ስሌት ይፈተሻል፡፡ በፍተሻውም የተገኘው ውጤት በመጠናዊ ገላጭ የምርምር ስልትና እንደ አስፈላጊነቱ አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ስታስቲክሳዊ ትንተና ተሰጠበታል፡፡ በመሆኑም የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ዝምድና ተፈትሾ ውጤቱ ተተንትኗል፡፡ ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎችም ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል አጥኝዋ ከጥናቱ የሚገኙ መረጃዎችን ለማመልከት ይቻላት ዘንድ በዋናነት መረጃውን ለመሰብሰብ የተጠቀመችበት ዘዴ ፈተና እና ለመምህራን የቀረቡ ቃለ መጠይቆችን ነው፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ የታቀፉ ተተኳሪ ተማሪዎች በቀረቡላቸው ሁለት የተለያዩ ፈተናዎች ያስመዘገቡት ውጤት ተንተርሶ የተሰበሰቡት መረጃዎች ለማመላከት የተሰሩበትን የስሌት ቀመር መሰረት በማድረግ ስታትስቲካዊ ገላጭ ትንተና ተሰጠባቸዋል፡፡

## 4.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች

አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነትን ለመለካት ያስችላሉ ተብለው የተሰጡ ሁለት ፈተናዎች በአቀራረባቸው ፈተና አንድ፣ አምስት የምርጫ ጥያቄዎች እና አምስት የእዉነት/ሀሰት ጥያቄዎችን አካቶ የቀረበ ሲሆን ፈተና ሁለትም እንዲሁ በተመሳሳይ አምስት የእውነት/ሀሰት እና አምስት የምርጫ ጥያቄዎችን እንዲይዙ ተደርገው የቀረቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ፈተናዎች በአጥኝዋና በረዳት መምህራን በጋራ ከታረሙ በኋላ በየግል ያስመዘገቡት ውጤት ተመዝግቦ እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በመነሳት እያንዳንዱ ተጠኝ ተማሪ በሁለቱ ፈተናዎች ያገኛቸው ውጤትና የሁለቱ ፈተናዎች አማካይ ውጤት እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ በዚህ መልክ የተመዘገበው ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡( አባሪ “4”ን ይመልከቱ፡፡

አባሪ “4” ያለው ሰንጠረዥእንደሚያሳየን በአንብቦ የመረዳት ፈተና አንድ የተመዘገበው ከፍተኛ ውጤት 10 ከ10 ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት 2 ከ10 (ሁለት ከአስር) ነው፡፡ የተጠኝ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አንድ አማካይ ውጤት 6.1 ሲሆን ይህ የሚያሳየን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ በአንቦቦ መረዳት ፈተና አንድ መደበኛ ልይይት 2.149564 ነው፡፡

በአንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት በተማሪዎች የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛው 10 ከ10 ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት 2 ከአስር ነው፡፡ የፈተና ሁለት አማካይ አንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤት 6.17 ሲሆን፣ መደበኛ ልይይት 2.268523 ነው፡፡ ይህም ከፈተና አንድ ጋር ተነፃፃሮ ሲታይ በተመሳሳይ መልኩ አብዛኛው ተማሪ ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት

ችሎታ ላይ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድና ሁለት አማካይ ውጤት 6.01 ሲሆን፣ መደበኛ ልይይት ነው፡፡ ከዚህ ተነስተን ከተገኘው ውጤት የምንረዳው በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ በጣም ጎልቶ የሚታይ ችግር መኖሩን ነው፡፡

የእያንዳንዱ ፈተና ዝርዝር ውጤት በተከታይ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.1.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና አንድ አንፃር

ሰንጠረዥ 1 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አንድ ውጤት

| ውጤት ከ10% | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 10 | 9 | 9 |
| 9 | 5 | 5 |
| 8 | 15 | 15 |
| 7 | 11 | 11 |
| 6 | 13 | 13 |
| 5 | 13 | 13 |
| 4 | 20 | 20 |
| 3 | 9 | 9 |
| 2 | 5 | 5 |
| 1 | 0 | 0 |
| ድምር | 100 | 100 |

ከተቀመጠው ሰንጠረዥ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ ውጤት ከ10% ከተፈተኑት ፈተና ውጤት ከፍተኛ ውጤት 10/10 ከአስር ሲሆን ዝቅተኛ ውጤት 2/10 ከአስር ነው፡፡ ከአጠቃላይ ቁጥር ውስጥ 60/100 ከመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች 6 እና ከዚያ በታች ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ 40 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ 7 እና ከዚያ በላይ ውጤት አምጥተዋል፡፡ ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በፍጥነት የሚያነቡ ሰዎች ወሳኝ በሆነ መልኩ ፈጣን የሆነ የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲኖራቸው

ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ ዝቅተኛ የመረዳት ችሎታ አላቸው በሚል በክለሳ ድርሳን ተገልጿል፡፡

### 4.1.2 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና ሁለት አንፃር

ሰንጠረዥ 2 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት ውጤት

| ውጤት ከ10% | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 10 | 9 | 9 |
| 9 | 8 | 8 |
| 8 | 13 | 13 |
| 7 | 13 | 14 |
| 6 | 15 | 15 |
| 5 | 20 | 20 |
| 4 | 9 | 9 |
| 3 | 8 | 8 |
| 2 | 5 | 5 |
| 1 | - | - |
| 0 | - | - |
| ድምር | 100 | 100 |

የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት እንደሚያሳየው የአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ከወሰዱ 100 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች መካከል ከ10 ከተፈተኑት ፈተና ከፍተኛው ውጤት 10 ከአስር ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት 2 ከአስር ነው፡፡ ከአጠቃላይ ተፈታኞች ውስጥ 57 ከመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች 6 እና ከዚያ በታች ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ 42 ከመቶ የሚሆኑ ደግሞ 7 እና ከዚያ በላይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ እዚህ ላይ ከፍተኛ ውጤት 10 ከአስር ሲሆን የተመዘግበው በ9 ተማሪዎች ብቻ ነው ይህ ከፍተኛ አንድ አንፃር ሲታይ ከፍ ብሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ዝቅተኛ ውጤት የተመዘገበው 2 ከአስር ሲሆን የተመዘገበውም በ5 ተማሪ ብቻ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ የምንረዳው አብዛኛው ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችግር ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ሁለቱን የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ስንመለከት በፈተና አንድ 60 ከመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች 6 እና ከዚያ በታች ሲያገኙ በፈተና ሁለት ደግሞ 57 ከመቶ የሚሆኑ ተማሪዎች 6 እና ከዚያ በታች ውጤት

አስመዝግበዋል፡፡ ይህ የሚያሳየን ውጤታቸው እምብዛም ያልተራራቀና ተቀራራቢ ከመሆኑ ባሻገር አንብቦ መረዳት ላይ ከፍተኛ ችግር መኖሩን የሚያመላክት ነው፡፡

### 4.1.3 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ

በክለሳ ድርሳን (Narayan's Warny (1995፣144-147) የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ሲገለፅ ከ10 ከታረመ ፈተና ከ9-10 ውጤት ያስመዘገቡ ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው፣ ከ7-8 ውጤት ያስመዘገቡ በቂ የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ከ5-6 ውጤት ያስመዘገቡ ዝቅተኛ ከ5 በታች ውጤት ያስመዘገቡ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተብለው እንደሚፈረጁ ይገልፃሉ፡፡

በዚህ ጥናት አቅራቢም ይህንን የምሁሩ አመዳደብ የሂሳብ ቀመር በመጠቀም ተማሪዎቹ በፈተናዎቹ ያስመዘገቡትን ውጤት ከዚህ በታች በቀረበው ወንጠረዥ አመላክታለች፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡ የተጠኚዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ አመላካች**

| ከ 10 % የስመዘገቡት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፈተና አንድ | | ፈተና ሁለት | | አማካኝ | |
| | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| ከ9-10 ያስመዘገቡ | 14 | 14 | 17 | 17 | 15.5 | 15.5 |
| ከ7-8 ያስመዘገቡ | 26 | 26 | 26 | 26 | 26 | 26 |
| 5-6 ያስመዘገቡ | 26 | 26 | 35 | 35 | 30.5 | 30.5 |
| ከ5 በታች ያስመዘገቡ | 34 | 34 | 22 | 22 | 28 | 28 |
| ድምር | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

ከላይ ከተቀመጠው ሰንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው ከ10% ከተፈተኑት ሁለት ፈተናዎች በአንብቦ መረዳት ውጤታቸው ከፍተኛ ቁጥር የያዙት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው ሲሆኑ፣ እነዚህም ከ5-6 እና ከ5 በታች ውጤት ያስመዘገቡት ናቸው፡፡ ከ7-8 እና ከ9-10 ያለውን ውጤት ያስመዘገቡት ደግሞ መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው፡፡ በፈተና አንድ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡት 60% ሲሆኑ በፈተና ሁለት ደግሞ 57% ናቸው፡፡ በፈተና አንድ ከ7 እስከ 8 ውጤት ያስመዘገቡት በቂ ደረጃ ላይ ያሉ አንባቢዎች ተብለው የተፈረጁት 26% ሲሆኑ፣ በፈተና ሁለት ደግሞ 26% ናቸው፡

፡ ፈጣን አንባቢዎች ብለን የምንፈርጃቸው ከ9 እስከ 10 ውጤት ያስመዘገቡ አንባቢዎች በፈተና አንድ 14% ሲሆኑ ፣ በፈተና ሁለት ደግሞ 17% ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ፈጣን አአንባቢዎች ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተብሎ በተመደበው ከ8-10 ያለውን ውጤት ያስመዘገቡት በአማካይ 15.5 ሲሆኑ 26% አንባቢዎች ደግሞ በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተብሎ በተመደበው ከ7-8 ያለውን ውጤት በአማካይ አስመዝግበዋል፡፡ 58.5%ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ ከ5 እስከ 6 እና ከ5 በታች የሆኑ ውጤት አስመዝግበው ይታያል፡፡ በመሆኑም በዚህ ሂሳባዊ ቀመር በተገኘው መረጃ መሰረት ፈጣን አንባቢዎች የምንላቸው በከፍተኛ አንብቦ መረዳት ደረጃና በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የሚገኙትንም የሚያካትት ሲሆን ዝግተኛ አንባቢዎች ብለን የምንፈርጃቸው ግን ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው አንባቢዎች የሚያመለክት ነው ተብሎ በተፈረጀው እርከን ላይ ተመዝግበው የሚገኙት ዝግተኛ አንቢዎች ስለሚያሳይ ነው፡፡ በጥናቱ እንደተመዘገበው ፈጣን አንብቢዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ሆኖ ቢስተዋልም ከዝግተኛ አንባቢዎች ይልቅ ፈጣን አንባቢዎች በተሻለ ሁኔታ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.2 የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ እና ፈተና ሁለት ዝርዝር መረጃ

የዚህ ጥናት ዋና የትኩረት አቅጣጫ ከሆነው ውስጥ አንዱ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥንት ያለበትን ደረጃ በጥናት አፈላልጎ የተገኘው የጥናት መረጃ በማመላከት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በዚህ ጥናት አጥኝዋ በጥናቱ ትኩረት ያደረገችው በሸካ ዞን ኩቢጦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ተማሪዎቹ አንድን ጽሁፍ ወይም ምንባብ ሲያነቡ በደቂቃ ምንያህል ቃላት እንደሚያነቡ ለማወቅ አጥኝዋ ለፈተና እንዲረዳት ባቀረበችው ምንባብ ላይ በማሳተፍ ያሉበትን ደረጃ ለመረዳት ተሞክሯል፡፡ በዚህ መሰረት ለተጠኝዎች የተሰጡት የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ( አባሪ “4”ን ይመልከቱ)፡

### 4.2.1 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና አንድ

**ሠንጠረዥ 4፡- የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና አንድ**

| የጥናቱ ተተኳሪ የንባብ ፍጥነት በፈተና አንድ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 118 | 10 | 10 |
| 102 | 8 | 8 |
| 90 | 4 | 4 |
| 85 | 6 | 6 |
| 78 | 12 | 12 |
| 70 | 20 | 20 |
| 62 | 18 | 18 |
| 58 | 15 | 15 |
| 55 | 3 | 3 |
| 50 | 4 | 4 |
| ድምር | 100 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ አራት የቀረበውን መረጃ ስንመለከው ንባብ ፍጥንት ፈተና አንድ ውጤት ከፍተኛው የንባብ ፍጥነት ወይም ፈጣን አንባቢዎች ያስመዘገቡት በደቂቃ 118 ቃላት ሲሆን ይህ ውጤት የተመዘገበው በ100 ተማሪዎች መካከል በአስር ተማሪዎች ብቻ ነው፡፡ ይህም ከአጠቃላይ ውጤት አንፃር ሲታይ 10% ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ዝቅተኛው የንባብ ፍጥነት ወይም ዝግተኛ አንባቢዎች 50 ቃላት በደቂቃ ያነበቡ ሲሆን ይህም በአራት ተማሪዎች ወይም 4% የተመዘገበ ውጤት ነው፡፡

በጥናቱ ከተካተቱ 100 ተማሪዎች መካከል 82 ከመቶው በደቂቃ ከ100 ቃላት በታች የሚያነቡ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም በተጠኝዎች የተመዘገበው የንባብ ፍጥነታቸው የሚያመላክተን ከክፍል ደራጃቸው አንፃር ሲታይ በጣም የወረደ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ

መሆኑን ያሳያል፡፡ ቀሪዎቹ 18 ከመቶ የሚሆኑት ከ102-118 ቃላት በደቂቃ ያነበቡ ቢሆንም በነዚህም የተመዘገበው ውጤት እንደሚሳየው የንባብ ፍጥነታቸው ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ የንባብ ፍጥነት አንድ አማካይ በደቂቃ 76.8 ቃላት ነው፡፡ በመሆኑም ከተገለፀው ውጤት አኳያ አብዛኛው ተማሪ በጣም ዝቅተኛ በሚባል ሁኔታ የንባብ ፍጥነት ላይ ያሉ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### 4.2.2 የተጠኝዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና ሁለት

በአባሪ "4" ሰንጠረዥ ላይ በንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት የተመዘገበው ዝቅተኛ ሰዓት 170 ሴኮንድ ወይም ፈጣን አንባቢዎች ምንባቡብ አንብበው ለመጨረስ የፈጀባቸው ሰዓት መሆኑን ሲያመለክት በተቃራኒው ከፍተኛ ሰዓት ያስመዘገቡ ወይም ዝግተኛ አንባቢዎች 414 ሴኮንድ ወስዶባቸዋል፡፡ የንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት 373 ቃላትን የያዘ ነው፡፡ ተጠኝዎቹ በመደበኛ ልይይቱም ይህንን አንብበው የጨረሱበት ጊዜ ተመዝግቦ ተይዟል፡ ፡ ከዚያም ምንባቡ የያዘው የቃላት ብዛት አንብበው ለመጨረስ በፈጀባቸው ጊዜ ተካፍሎና በስድስት ተባዝቶ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

**ሰንጠረዥ 5፡- የተጠኝ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና ሁለት**

| የጥናቱ ተተኳሪ የንባብ ፍጥነት በደቂቃ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 140 | 4 | 4 |
| 135 | 5 | 5 |
| 125 | 9 | 9 |
| 110 | 6 | 6 |
| 105 | 6 | 6 |
| 95 | 12 | 12 |
| 90 | 21 | 21 |
| 84 | 12 | 12 |
| 80 | 15 | 15 |
| 55 | 10 | 10 |
| ድምር | 100 | 100 |

የንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት ውጤት እንደሚያመለክተው 70 ከመቶ የሚሆኑት የጥናቱ ተተኳሪ ታሪዎች ከ100 ቃላት በታች በደቂቃ ያነበቡ ሲሆኑ 30 ከመቶ የሚሆኑ ደግሞ ከ100 ቃላት በላይ በደቂቃ አንብበዋል፡፡ ከተጠኝዎቹ መካከል ከፍተኛ / ብዛት ያለው/

ቃላት በደቂቃ ያነበቡት ፈጣን አንባቢዎች ተብለው የተገለፁት 140 ቃላት በደቂቃ ሲሆን፣ እነዚህም በቁጥር አራት ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ ይህም ከአጠቃላይ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አራት ከመቶውን ብቻ ይይዛሉ፡፡

የንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለትን አማካይ ውጤት ስንመለከት 101.9 ቃላት በደቂቃ ማንበብ መቻላቸውን እንረዳለን፡፡ ይህ ከጥናቱ ተተኳሪዎች የተገኘው መረጃ ከወዲሁ የሚያሳየን አብዛኛው ተማሪ በጣም ዝቅተኛ ተብሎ መጠቀስ በሚችል መልኩ ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት ደረጃ ላይ ያሉ መሆናቸውን ወይም ዝግተኛ አንባቢ ተብለው በሚፈረጀው ደረጃ ላይ ያሉ መሆናቸውን ያመላክተናል፡፡ ሆኖም የፍጥነት ንባብ ማሻሻል አይቻልም ከሚለው ፍረጃ አያደርሰንም፡፡

### 4.2.3 የፈተና አንድና ሁለት አማካይ የቃላት ብዛትና የማንበብ ፍጥነት

**ሠንጠረዥ 6፡- የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አማካይ የንባብ ፍጥነት የሚያሳይ መረጃ**

| የምንባቦቹ አማካይ የቃላት ብዛት | ምንባቡን ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሰኮንድ | ድግግሞሽ | መቶኛ | ጠቅላላ ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|---|
| 359 | 160 | 4 | 4 | 4 |
| | 165 | 5 | 5 | 9 |
| | 179 | 9 | 9 | 18 |
| | 203 | 6 | 6 | 24 |
| | 235 | 6 | 6 | 30 |
| | 263 | 10 | 10 | 40 |
| | 280 | 20 | 20 | 60 |
| | 302 | 11 | 11 | 71 |
| | 319 | 14 | 14 | 85 |
| | 406 | 9 | 9 | 94 |
| | 447 | 6 | 6 | 100 |
| | ድምር 28542.5 | 100 | 100 | 100 |
| በመደበኛ ልይይት | አማካይ 285.42 | | | |

የተጠኚዎች ብዛት 100

የምንባቡ አማካይ የቃላት ብዛት 359

ምንባቡን አንብቦ ለመጨረስ ፈጀው አማካይ ሰዓት 285.42

መደበኛ ልይይት

በአጠቃላይ በሠንጠረዥ የተመለከተው የማንበብ ፍጥነት Nuttal (1982,34) ቀመር መሠረት ሲሰሳ የሚገኘው ውጤት 76.5 ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች በአማካይ 76 ቃላትን በደቂቃ እንደሚያነቡ ያመላከታል፡፡

X x 6 =Y------ x6 =Z

በሁለቱም የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡትን ስንመለከት በንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ 50 ቃላት በደቂቃ ያነበቡ አራት ተማሪዎች ሲሆኑ በንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት ደግሞ 55 ቃላት ያነበበው ተማሪዎች 10 ነው፡፡

ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር እየቀነሰ ቢመጣም እንኳ የንባብ ፍጥነት አሁንም ከሚፈለገው ደረጃ በታች ላይ ያለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሁለቱ የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች ማለትም በንባብ ፍጥነት ፈተና አንድና በንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት አማካይ የተመዘገበው ሰዓት ሴኮንድ ሲሆን በNuttal (1982,) የሰሌት ቀመር ሲሰላ የሚያሳየን አብዛኛው ተማሪ ወይም 80 ከመቶ የሚሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ አብዛኛው ተማሪ የፍጥነት ንባብ ችግር ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡

## 4.3 አፍ መፍቻ ቋንቋ ከ አንብቦ መረዳት ችሎታና ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለው ግንኙነት

የዚህ ጥናት ንዑሳን አላማዎች አንዱ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አንፃር ማጥናት እንደሆነ ይታወቃል፤ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የታቀፉ 100 ተማሪዎች ሁሉም አፋቸውን በሽክኛ ቋንቋ የፌቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ብቻ አካቶ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አንፃር ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል፡፡ የተገኘውም ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በተጠኝዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥንት መካከል ቀጥተኛ በሆነ መንገድ አሉታዊ የሆነ ተዛምዶ እንደሚታይ ስታስቲከሳዊ መረጃው ያመለከታል፡፡ ይህም ማለት የተጠኝዎች የንባብ ፍጥነት ሲቀንስ በዚያው ልክ የአንብቦ መረዳት ችሎታም መቀነስ እንደሚያሳይ ተረጋግጧል፡፡በዚህ መሰረት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ የማንበብ ፍጥነት እና የማንበብ ብቃት በአዝጋሚ ደረጃ ላይ መገኘት ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸው በዝቅተኛ

ደረጃ ላይ መሆን እንደ አብይ ችግር ሊቆጠር የሚችል ጉዳይ መሆኑን መገመት ተችሏል፡ ፡ የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማደረግ እና በክለሳ ድርሳናት በመታገዝ የመረጃ መፍትሂ ሀሳቦች ተመላከተው ጥናቱ ተጠቃሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 7የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ጋርያለው ግንኙነት**

| የተጠኝ ተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ | በደቂቃ የሚያነቡት የቃላት ብዛት በአማካይ | አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና በአማካይ ውጤት ከ10% |
|---|---|---|
| በሽክኛ | 88% | 5.9% |

## 4.4 የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ ግንኙነት

በንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ ፈጣን አንባቢዎች 118 ቃላትን በ170 ሴኮንድ ያነበቡ ሲሆን ዝግተኛ አንብቢዎች ደግሞ በ414 ሴኮንድ አንብበዋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና አንድ ውጤትን ስንመለከት ከፍተኛው አስር ከአስር ሲሆን ዝቅተኛው 2 ከአስር ነው፡፡ አስር ከአስር ውጤት የተመዘገበው በፈጣን አንባቢዎች ሲሆን 2 ከአስር የተመዘገበው በዝግተኛ አንባቢዎች ነው፡፡ የንባብ ፍጥነት ሲቀንስ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ይቀንሳል፣ እንዲሁም ለማንበብ የፈጀው ሰዓት ሲቀንስ አንብቦ የመረዳት ችታ ውጤት ይጨምራል ማለት ነው፡፡ ከዚህ መሪ ሀሳብ የምንረዳው የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተደጋጋፊ መሆናቸውን ነው፡፡

## 4.5 የንባብ ፍጥነትና አንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ግንኙነት

የንባብ ፍጥነትና አንብቦ መረዳት ፈተና ሁለትን ውጤት ዘርዘር ባለ መልኩ ስናስቀምጠው ፈጣን አንባቢዎች 345 ቃላትን በ170 ሲኮንድ ሲያነቡ ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ 414 ሴኮንድ ወስዶባቸዋል በአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ከፍተኛ ውጤት 10 ከአስር ሲሆን የተመዘገበውም የፈጣን አንባቢዎች ነው፡፡ ዝግተኛ አንባቢ ደግሞ ከአስር ከ2 እስከ 3 ያለውን ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በዚህ መሰረት ፈጣን አንባቢዎች ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳላቸው ከወዲይሁ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያያዘ መልኩ በአንብቦ መረዳት እና በንባብ ፍጥንት መካከል ከፍተኛ ትስስራዊ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ መኖሩን ነው፡፡ በዚህም ለማንበብ የፈጀው ሰዓት ሲቀነስ አንብቦ መረዳትም ችሎታ የሚጨምር

መሆኑንና በተቃራኒው ለማንበብ የፈጀው ሰዓት ሲጨምር አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚቀንስ መሆኑን እንረዳለን፡፡

## 4.6 በንባብ ፍጥነት በአንብቦ የመረዳት መካከል ያለው ተዛምዶ

በንባብ ፍጥንትና በአንብቦ መረዳት መካከል ያለው የተዛምዶ በSPSS የኮንፒውተር ፕሮግራም በመጠቀም በባለሙያ ድጋፍ ተሰርቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ላይ በማኖር እንዲመላከት ተደርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 8 በንባብ ፍጥነትና በአንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶየሚያሳይ**

| | የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተና 1 | የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተና 2 | አማካይ |
|---|---|---|---|
| አንብቦ የመረዳት ፈተና 1 | 0.071312 | | |
| አንብቦ የመረዳት ፈተና 2 | | 0.079763 | |
| አማካይ | | | 0.075466 |

የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን በፍጥነት ንባብና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ጥብቅ የሆነ ቁርኝት ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የፍጥነት ንባብና አንብቦ መረዳት ችሎታ ቁርኝት ውስብስብ መሆኑን በመጥቀስ እነዚህ ሁለት ንዑሳን ክሂሎች በአንድነት መዳበር እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

Nutta ( 2000፡54) እና Anderson (1992፡2) አንባቢዎች የንባብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር በሚያደርጉት ተከታታይነት ያለው ጥረት የንባብ ፍጥነታቸውን በማሻሻል ብቁ አንባቢ ሊሆኑ እንደሚችሉና በፍጥነት ንባብና የአንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከልም የጎላ ትስስር እንዳለ ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ጥናታዊ የምርምር ስራም በእነዚህ በሁለቱ ንዑሳብ የንባብ ክሂሎች መካከል ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም በጥናቱ በታቀፉ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ የተገኘው ውጤት 0.075466 እንደሆነ ታውቋል፡፡ ይህ የሚያሳየን የሁለቱም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች መካከል ያለውን የርስ በርስ የግንኙነት ዝምድና ተነጣጥለው ሊታዩ የማይችሉ መሆኑን ነው፡፡ ከላይ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት 0.075466 በተማሪዎች የንባብ ፍጥነት አንብቦ

የመረዳት ችሎታ መካከል ያለው ዝምድና ጠንካራ አሉታዊ ዝምድና ነው፡፡ ለማንበብ የሚፈጀውን ሰኮንድ ሲጨምር አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በእጅጉ ይቀንሳል በተቃራኒ ነው ለማንበብ የሚፈጀውም ሴኮንድ ሲቀነስ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ይጨምራል፡፡ ይህንን ሃሳብ ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስቀመጥ ስንሞክር ፈጣን አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ ሲሆን ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ በዚህም የተማሪዎች የፍጥነት ንባብ ችሎታ ከፍ ሲል / ሲያድግ/ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው አብሮ እንደሚያድግ ያሳያል፡፡

## 4.7 ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

አጥኝው ለዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኖ እንዲያገለግለው የመረጃ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ መረጃም በሚከተለው መልኩ በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ (አባሪ 5 ይመልከቱ)

**ሠንጠረዥ 9 ለቃለ መጠይቅ የተሳተፉ መምህራን አጠቃላይ መረጃ የሚያሳይ**

| የመምህራን ብዛት | ጾታ | | የትምህርት ደረጃ | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | | |
| | 2 | 1 | የመጀመሪያ ዲግሪ | 9-38 ዓመት |

ከሠንጠረዥ አንድ ምንረዳው ቃለ መጠየቅ የተደረገላቸው መምህራን በቁጥር 3 ሲሆኑ 2 ወንድ እና 1 ሴት መምህራን ናቸው፡፡ የትምህርት ደረጃቸውም 3 ፣ቱም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን የአገልግሎት ዘመናቸውም የመጀመሪዉ 9 አመት፣ ሁለተኛዋ መ/ር 28 ዓመት እና ሦስተኛም መ/ርት ደግሞ 38 አመት ያገለገሉ ናቸው፡፡

## 4.7.1 የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታንና

## የንባብ ፍጥነትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከመምህራን በቃለ መጤቅ አማካይነት የተገኘው ምላሽ በፈተና አማካይነት የተገኘውን ውጤት ሙሉ በሆኑ መልኩ የሚደግፍ ነው፡፡ ይህም

- የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው?
- ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎች ለይተው ያውቃሉ?

- ከፈጣንና ከዝግተኛ አንባቢዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው የትኞዎች ናቸው?

ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄዎች መምህራኑ ምላሽ ሲሰጡ ሶስቱም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደሆነና ችግሩ ከትምህርት ቤት ባለፉ እንደ ሀገር አሳሳቢ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችግር የመነጨውም በተለይ ከታችኛው ክፍል ደረጃ ጀምሮ ፊደል ለይቶ ያለመምጣት እና ያለብቃት ከክፍል ወደ ክፍል እንዲሸጋገሩ መደረጉ፣ በተለይ ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ስንከተለው የነበረው የትምህርት ፖሊሲ ብቃት የሌላቸውን ተማሪዎች ወደ ተከታይ ክፍል እንዲሸጋገሩ መፍቀድ፣ ተማሪ በግል የንባብ ችሎታውን ለማሳደግ ጥረት ያለማድረግ እና የተነሳሽነትና የፍላጎት እጦት፣ እንዲሁም ንባብን በተገቢው ለመተግበር በቂ የሆነ የክፍለ ጊዜ ምደባ አለመኖር ተገልፀዋል፡፡ ከዚህም ጋር አያይዘው ወደ ተከታይ ጥያቄዎች ሲያመሩ ማለትም ሰሶስቱም በተመሳሳይ ሁኔታ ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለይተው ለማወቅ ያደረጉት ጥረት እንደሌለና ካለን የሙያ ልምድና እኛም ቀድመን ከቀሰምነው ትምህርት አኳያ ፈጣን አንባቢዎች ከዝግተኛ አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው በማለት ገልፀው ከመካከላቸው አንዱ በክፍል ውስጥ ጥቂት ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ሲያነቡ አብዛኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ለማንበብ ካለመቻላቸው የተነሳ ተማሪዎች ተነስተው ለማንበብ ፍቃደኛ ያለመሆናቸው አስተውያለው በማለት መልሰዋል፡፡ ሌላው መ/ር የተሻለ የማንበብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚያሳዩት ተሳትፎና አረዳድ አኳያ ፈጣን ተማሪዎች ከዝግተኛ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው መሆኑን እረዳለሁ ሲሉ መልሰዋል፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም ከፈተና በተገኘው ውጤት ያረጋገጠችው የፈጣን አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከዝግተኛ አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ የተሻለ መሆኑን ነው፡፡

## 4.7.2 የመምህራን ክትትልን የራስ ጥረትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ያዳብሩ ዘንድ መምህራን ምን አይነት ክትትል የሚያደርጉ መሆናቸውን ለማወቅ ለመምህራኑ የሚከተሉት መጠይቆች ቀርበውላቸዋል፡፡ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ለማሳደግ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? የሚል መጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን ከሁሉም ተጠያቂ መምህራን የተገኘው ምላሽ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ለማዳበር ብለው ሌሎች ምንባቦችን ሲያነቡ አይስተዋሉም፡፡ ከማስተማሪያ መጽሃፍ ላይ የሚሰጧቸውን ምንባቦች አንብበው የመልመጃ ጥያቄዎችን የሚሰሩ ተማሪዎችም በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ፈፅሞ ተነሳሽነት አይታይባቸውም ሲሉ ገልፀዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ያላቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ዝቅተኛ ደረጃ ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በመቀጠል የተማሪዎችን አንብቦ የመዳት ችሎታና የንባብ ፍጥንት ለማዳበር ምን መደረግ አለበት? ለሚለው ጥያቄ ሦስቱም መምህራን ሀሳባቸው ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን በተለይ ሁለቱ ዋናው የንባብ መሰረት የሚጀምረው ከቤት ውስጥ ስለሆነ ህፃናቱን ወደ ት/ቤት ስንልክ አያይዘን በቤት ውስጥ እገዛ በማድረግ መጽሃፍቱን ገዝተን እያነበብንላቸው ተነሳሽነትን እንዲያመጡ ቢደረግ፣ በንባብ ክፍለ ጊዜ ለተማሪዎች በቂ ክትትልና ድጋፍ ቢደረግ፣ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ መሻሻል ቢደረግበት ፣ በንባብ ክሂልና በማስተማር ስነ ዘዴ ዙሪያ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ቢሰጥ እንዲሁም በወላጅ፣ በት/ቤትና በመምህራን መካከል ያለው የትስስር ግንኙነን ቢጠናከር  በማለት መልስ የሰጡ ሲሆን አንዷት መ/ርት ግን ከዚሁ ሃሳብ ላይ አክላ በምታስተምርበት  ት/ቤት አብዛኛውን ተማሪ ኢ-አፌፌት የሆኑ ተማሪዎች መሆናቸውን ገልፃ በነዚህ ተማሪዎች ላይ ከልጅነታቸው ጀምሮ ስለ አማርኛ ቋንቋ ሲደረግላቸው የነበረው ጥላቻና መጥፎ አመለካከት አብሯቸው ያደገ በመሆኑ ይህን በመቅረፍ ዙሪያ ላይ ከፍተኛ የሆነ ስራ ሊሰራ ይገባል ሲሉ ገልፁዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለቀረቡላቸው ሁለት ጥያቄዎች ማለትም የንባብ ትምህርትን ለማደበር የሚቻለው በቋንቋ መምህራን ላይ ብቻ ሳንወስን የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን በሚያስተምሩ መምህራን የጋራ ጥረትና ርብርቦሽ ነው ሲባል በተሰነዘረው ሃሳብ ይስማማሉ? ለሚለው መጠይቅ ሦስቱም መስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡አያያዘውም ሲገልፁ

የቋንቋ ትምህርት ችግር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ችግር ብቻ አይደለም የሚፈታውም በነሱ ብቻ ሳይሆን የሌሎችም መመህራን ተሳትፎን ይጠይቃል፡፡ ይኸውም ሁሉም ትምህርቶች በጽሁፍ ተቀናብረው ቢቀርቡም ብሎም የራሳቸው አካሄድ ያላቸው ቢሆኑም ውስጣዊ ይዘታቸውን ፈትሾ ለመረዳት አንብቦ መረዳት ግድ ይላል፡፡ ስለዚህ የሙያው ባለቤቶችም ሆኑ የሚመለከታቸው ክፍሎች ትኩረት ሰጥተው ሊረባረቡበት ይገባል፡፡ ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመጨረሻም ለቀረበላቸው ጥያቄ ማለትም የተማሪዎች፣ የንባብ ችግር ለመቅረፍ ከተማሪ ወላጆች ጋር ተገናኝቶ በመወያየት በኩል ምን ያህል ተጉዘዋል? ለሚለው መጠይቅ ምላሽ ሲሰጡ ሦስቱም በመጠይቁ መሠረት ላይ ያተኮረ ቀጥተኛ ተሳትፎ ባናደርግም ተማሪዎች የተሰጣቸውን የቤት ስራ ሳይሰሩ ሲቀሩ፣ በቅጥር ግቢ እያሉ ክፍል ገብተው ትምህርት ሳይከታተሉ ሲቀሩና በቀሪ ማብዛት ሳቢያ ወላጅ እንዲያመጡ በማዘዝ በተማሪው ዙሪያ ያለውን ችግር እንዲያውቁ በማድረግ በኩል ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን በማለት ገልፀው አያይዘው ተማሪው ያለበትን የንባብ ችግርም ወላጅ እንዲረዳው እናደርጋለን ሲሉ ሦስቱም በተመሳሳይ ሁኔታ ገልፀዋል፡፡ የዚህጥናት ዉጤት የሚያመለክተው በንባብ ፍጥነትላይ ፈጣን አንባቢዎች ያስመዘገቡት ውጤት በደቂቃ አንድ መቶ አስራ ስምንት ቃላት ሲሆን ይህ ዉጤት የተመዘገበው ከመቶ ተማሪዎች መካከል በአስር ተማሪዎች ብቻነው፡፡ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ ሀምሳ ቃላትን በደቂቃ ማንበብ ሲችሉ ከመቶ ዘጠናዎቹ ናቸው፡፡በመሆኑም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑን ያሳያል፡፡ምክንያቱምንባብ ፍጥነትከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ከፍተኛ የሆነ ዝምድና እንዳለዉጥናቱ አመላክቷል፡፡

## 4.8 የዉጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሸክኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት መካከል የሚታየው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል መመርመር ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት ጥናቱ ሦስት መሰረታዊ ጥያቄወችን መመለስ ሞክሯል፡፡አንደኛ የሸክኛቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይይገኛል የሚል ሲሆን በጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ተተኳሪ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት በፈተና አንድ ከፍተኛው 10 ከ10 ሲሆን ዝቅተኛው 2 ከ10 እንደሆነ አመላክቷል፡፡ ከፍተኛ ያመጡ ተማሪዎች ብዛት በአማካይ 15.5% ብቻ ሲሆኑ ሌሎች ዝቅተኛ ያመጡ ተማሪዎች ብዛት በአማካይ 28% ናቸው፡፡

በአንብቦ መረዳት ፈተናው የተመዘገበው ውጤት 2፣3፣እና 4 ከ10 ሲሆን ከፍተኛው 10ከ10ነው፡፡ ይኸውም አብዛኛው ተማሪ ዝቅተኛ አንብቦ መረዳትችሎታ ላይ የሚገኝ መሆኑን የጥናቱ ግኝት አሳይቷል፡፡

ለሁለተኛው ጥያቄ በሸክኛ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የ9ና ክፍልአማርኛቋንቋ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት ምን ይመስላል የሚል ሲሆን  የተገኘው  ውጤት በሁለቱም የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች ዝቅተኛ ውጤት ያየስመዘገቡት በፈተና አንድ 50 ቃላት በደቂቃ ያነበቡ ተማሪዎች 6ናቸው ፡፡ይህም ውጤት የሚያሳው በተጠኝዎች ዘንድ ከፍ ያለ የንባብ ፍጥነት ችግር መኖሩን ነው፡፡በሁለቱ የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች ማለትም በንባብ ፍጥነትፈተና አንድና በንባብ ፈጥነትፈተና  ሁለትማካይውጤት የተመዘገበው ሰአት285.42     ሲሆን በ Nuttal (1982) የስሌት ቀመር ሲሰላ የሚያሳየን አብዛኛው ተማሪ 80 ከመቶ የሚሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት እንዳላቸው ይገልጻል፡፡

ከዚህ ጥናትውጤት ጋር በሚገናዘብ መልኩ ፣በረከት፣(2010)፣አያሌው(2001)፣ተሾመ(2007) ባቀረቡት ጥናትበተመሳሳይ ሁኔታ እንዳመለከቱት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡እንዲሁም የንባብ ፍጥነታቸው ዝግተኛደረጃ ላይ እንደሆነ ታውቋል፡፡በዚህም በአንብቦ መረዳትችሎታና በንባብ ፍጥነት መካከል ተዛምዶ መኖሩ ተረጋግጠዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡በተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና ችሎታና የንባብ ፍጥነት መካከል ጉልህ ተዛምዶ አለ፡፡የተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ጋር ዝምድና መኖሩን አሳይቷል፡፡ ይህም ማለት የንባብ ፍጥነታቸው ሲጨምር የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውም በተመሳሳይ ይጨምራል፡፡ የተማሪዎቹ የንባብ ፍጥነት ሲጨምር አንብቦየመረዳት ችሎታቸው ውጤተ በጉልህ ደረጃ ስለሚጨምር፣ በሁለቱ መካከል የጠበቀ ግንኙነ ይታያል፡፡ ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ያላቸው የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው፡፡ለዚህም ፡- በሸክኛ አፍ ፈትየሆኑ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ትምህርትለመማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆንየየትምህርት ፖሊሲ ለትምህርቱ ጥራት የሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆን ተማሪዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሲሸጋገሩ ተገቢውን የንባብ ችሎታ ይዞ አለመምጣት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትእና ትኩረት ዝቅተኛ መሆን የተማሪዎች የንባብ ባህል ዝቅተኛ መሆን የራሳቸውን የንባብ ልምድ ለማሻሻል ጥረት ያለማድረግና የቤተሰብ ክትትልና ተገቢ ድጋፌ ያለመኖር የሚሉት ለአንብቦ መረዳትና ለንባብ ፍጥነት ዝቅተኛ መሆን በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

## 5.2 ማጠቃለያ

- የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ ወይም የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ ከጅምር መነሻው እስከ ጥናቱ ማብቂያ መዳረሻ ድረስ ተመርኩዞ የዘለቀው ሸካ ዞን በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸከኛ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡
- ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ከመነሻ እስከ መድረሻ ማዝለቅ የሚያስችሉ አብይና ዝርዝር አላማዎች በምዕራፍ አንድ፣የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አብይና ዝርዝር አላማዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ በምዕራፍ ሁለት ስለንባብ ምንነት፣ ስለ አንብቦ መረዳት ችሎታ ምንነት፣ በፍጥነት ንባብ ምንነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍጥነት ንባብ ጋር

ያለውን ተዛምዶና ምሁራን ያነሷቸውን ሃሳቦችና ያደረጓቸውን ጥናቶች በማስደገፍ ተዘርዝሮ ቀርቧል፡፡

- በምዕራፍ ሶስት፡- ለጥናቱ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ የቀረበው ፈተና፣ ለመምህራን ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃና መረጃው እንዴት እንደሚተነተን በዝርዝር ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አራት ደግሞ በፈተና የተሰበሰበው መረጃ ተተንትኖ ውጤቱ የተገለፀ ሲሆን፣ ከመምህራን ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃም የአይነታዊ የምርምር ዘዴ በሆነው በገላጭ የአተናተን ዘዴ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በነዚህ መተንተኛ ዘዴዎች ከተገኘው ውጤት በመነሳት የሚከተለው የማጠቃለያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡
- አብዛኛው ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችሎታው ዝቅተኛ ወይም ከሚጠበቀው ደረጃ በታች መሆኑን ማወቅ ተችሏል፡፡ ይኸውም ከግማሽ በላይ 60% ያህሉ ከአስር ከታረመው ፈተና ከ5-6 እና ከ5 በታች ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ የህ የሚያሳየን አብዛኛው ተማሪ የንባብ ፍጥነታቸው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ እንደዚሁም አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸው ከዝግተኛ አንባቢዎች የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- ይህ ከላይ የተቀመጠው ሃሳብ በአንብቦ መረዳትና በፍጥነት ንባብ መካከል ዝምድና መኖሩን ያሳያል፡፡ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነት ለማወቅ በተሰጠው ፈተና ተማሪዎቹ በአማካይ በደቂቃ 88 ቃላትን እንደሚያነቡ የታወቀ ሲሆን ይኸም ከላይ የቀረቡ ሃሳቦችን ጠቅለል ባለ መልኩ ሲቀመጡ ጥናቱ በስተመጨረሻ ላይያስገኘው ውጤት የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ከፍተኛ የተዛምዶ ያላቸው መሆኑን የረጋገጠ ሲሆን የተካሄደው ጥናትም የጥናቱን ዋነኛ ርዕስ የመሰለ በመሆኑ Nuttal (1982:33) የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑን ምሁራኑ ባስቀመጡት የጥናት ሃሳባቸው ከክፍል ደረጃቸው አንፃር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም ያላቸው የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረደት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው ለዚህም ከተጠቀሱ ነጥቦች መካከል፡-
- ተማሪዎች በአማርኛ ሆሄያትን በ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እየተማሩ በነበሩበት ወቅት ሳያጣሩ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሲሸጋገሩ ለንባብ የሚያበቃ ብቃት ይዘው አለመምጣት
- ተማሪዎች የራሳቸውን የንባብ ልምድ ለማሻሻል ጥረት ያለማድረግ
- በቂ የልምምድ ጊዜና ተገቢ ድጋፍ ያለመኖር

- ተማሪዎች በየግል የንባብ ችሎታውን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማምጣት የሚያሳዩት ተነሳሽነት አለመኖር
- ኢ-አፊፊት ተማሪዎች በቋንቋው ተምረው ለመጠቀም ያላቸው ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ ይጠቀሳሉ

## 5.3 አስተያየት

ዛሬ ዛሬ አለማት የደረሱበትን የቴክኖሎጂ ዕድገትና ውጤቶች እንዲሁም የሳንሳዊ ግኝቶችን ምንነት ማወቅና መረዳት የምንችለው አንብበን መረዳት ስንችል መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ በተገቢው አንብበን መረዳት አለመቻል ማለት ዓለማት ደረሱበትን የዕድገት ደረጃና ስልጣኔ መድረስ አለመቻል መሆኑን ልንረዳ ይገባል፡፡ ስለዚህ ዓለማት ከደረሱበት የስልጣኔ ደረጃ መድረስ እንድንችል ንባብን ዋና ቁልፍ መሳሪያ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የንባብ ስልታችንንም በፍጥነት ማንበብና አንብቦ መረዳትን በሚያጎለብት መልኩ ቢሆን ውጤታማ ያደርገናል፡፡ ከዚህ ጥናትም የምንጨብጠው ግንዛቤ ይህንኑ ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ከማችሉ ነጥቦች መካከል፡-

- በአማርኛ አንብቦ የመረዳትና የንባብ ፍጥነት ለማሻሻል የሚያግዙ የማስተማሪያ ስነ ዘዴዎች ተግባራዊ የሚደረጉበት ሁኔታ ቢመቻችና ለንባብ ክሂል ትኩረት ቢሰጥ፣
- ለመምህራን ተማሪዎች የማንበብ ልምዳቸውን እንዲያጎለብቱ በክፍል ውስጥ ከሚማሩት ውጪ በትምህርት ቤቱ  መጻህፍት ቤት ገብተው ሌሎች ምንባቦችን እንዲያነቡ ቢያበረታቷቸው፣
- ለመምህራን በማንበብ ክሂል ላይ በጥልቀት ለውጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ ተከታታይ ስልጠና ቢሰጥ፣
- የቋንቋ መማሪያ መጽሃፍት ሲዘጋጁአንብቦ የመረዳት ችሎታን በሚያዳብር መልኩ የንባብ ፍጥነት ስልትን ተግባራዊ እንዲሆን በሚያደርግ መልኩ የሚዘጋጅበት ስልት ቢመቻች፣
- በተማሪዎች በኩል የሚፈጠሩ የተለያዩ ትምህርታዊ ችግሮች ለመቅረፍ በወላጅ በመምህራንና በትምህርት ቤት አስተዳደር መካከል ያለ ግንኙነት ያበልጥ እንዲጎለብት ቢደረግ፣

- ወላጆች የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ለማሳደግ እንዲቻል በቤት ውስጥ ለልጆቻቸው መጻሕፍትን ገዝተው በማቅረብ ተነሳሽነታቸውን ከፍ የሚያደርጉበት ሁኔታ ቢመቻች፣
- የተማሪዎች የንባብ ፍጥነት ለማወቅ በተሰጠው ፈተና ተማሪዎች አማካይ በደቂቃ ምን ያህል ቃላት እንደሚያነቡ የታወቀ ሲሆን የንባብ ፍጥነታቸው ከክፍል ደረጃቸው አንፃር፣ የሚመጥን መሆኑን መገምገም ቢቻል፣
- የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከአንብቦ መረዳት ችሎታና ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለውን ተዛምዶ በተከታይ በጥልቀት በጠና የተሸለ ለውጥ ይመጣል የሚል እምነት አለኝ፡፡
- የአገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ የአካሄድ አቅጣጫው በየጊዜው እየተፈተሸ መሻሻል ያለበት እየተሻሻለ መሄድ በሚችልበት መልኩ የሚተገበርበት ሁኔታ ቢመቻች ችግሮቹ
- ሊቀረፉ ስለሚችሉ ለአተገባበሩ ምቹ ሁኔታዎች ከወዲሁ ቢመቻቹ የተሻለ ነው፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ ትምህርት ችግር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ችግር ብቻ አለመሆኑና ችግሩ የሚፈታውም በነሱ ብቻ ሳይሆን የሌላ ትምህርት ባለቤት የሆኑ መምህራን ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይኸውም ሁሉም ትምህርቶች በጽሑፍ ተቀናብረው የሚቀርቡና የየራሳቸውም የአተገባበር ሂደት ያላቸው ቢሆኑም የየትምህርቶቹን ውስጣዊ ይዘቶች ፈትሾ ለመረዳት ይቻል ዘንድ አንብቦ መረዳት ግድ ይላል፡፡ ስለዚህ የሙያው ባለቤቶች ከወዲሁ ሊረዱት የሚገባ ጉዳይ ተማሪው የአንብቦ መረዳት ብቃቱ ዝቅተኛ ነው ማለት የሚያስተምሩትን ትምህርቶች በውል መረዳት አልቻሉም ማለት መሆኑን አጢነው የጋራ የሆነ ርብርቦሽ ሊያደርጉ ይገባል የሚል እምነት አለኝ፡፡

## ዋቢዎች


መኮንን፡፡(2000)፡፡ “በአዊኛ አፋቸውን የፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ግምገማ፡፡” ለሁለተኛ ደግሪ ማማያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ ( ያልታተመ)፡፡

ትምህርት ሚኒስተር (2007)፡፡ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህራን ማሰሌጠኛ ማንዋሌ፡፡ አዱስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስተር

ተሸመ ፎርሲዶ ፡፡ (1997) ፡፡ “በከምባታ ጠምባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታቸውና የማንበብ ፍጥነታቸው፡፡” ለሁለተኛ ደግሪ ማማያ የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

በረከት ሁሴን (2010)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሡገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በሡገን ሁለተኛደረጃና መሰናድ ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢአፍፊት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችልታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት

አያሌው አንተነህ ፡፡ (2001)፡፡ “በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአንባቦ የመረዳ ክሂል ጋር ያለው ተዛምዶ በወልዲያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተመሠረተ ጥናት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ ፡፡ (1998)፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችንና አቀነባበር፡፡ ባህዳር፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዮሐንስ ሰለሞን፡፡ (2013) ፡፡በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፊት የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ትንተና በጉጂ ዞን በነገሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተመሠረተ ጥናት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡ጅማ ዩኒቨርሲቲ

Alderson, J. C (2000). Assessing Reading Cambridge Cambridge University Press.

Alderson, N.J. (1999). “ Improving Reading speed Activities for Class room” English Teaching Forum Vol.37 no. 2 april Anderson r.c etal ( 1988)

Growth in Reading and How children spend their Time out side of school Reading Research Quarterly , 23(3) pp 285-303 http/www.twe boread com/.

Bell, T. ( 2001) " Extensive Reading speed and comprehensi on" The Reading

Materix Vol. 1 No 1 April http//wwwReading matrix com/ Articles /bell index htm.

Fry, E. ( 1963) Reading Faster: a Drill Book Cambridge Eambride University Press.

Grabe, W. and LF . stoller ( 2002) . Teaching and Researching Reading Hariow pearson Education.

Green Wood, J ( 1981). " compensation and Reading". In Abbottg and wingard, P. (eds) Teaching of English as are international Language , A practicalGuid Oxford Oxforde University press.

Grellet, F ( 1981) . Developing Reading skills. A practical Guide to Reading Cpmprehensive Exercise ) 1st ed). Cambridge Cambridge Unicersity press.

--------- ( 1996), Developing Reading skills cnmbrudge Cambridge Unicersity Press.

Heaton, J. B (1975) Writing Language Tests A Practical Guide for teachers of English as second Language foreign language London: Longman.

Hughes, A ( 1989) Testing for language Teachers cnmbrudge Cambridge Unicersity Press.

Madsen H.S . ( 1983) . Techniques in Testing New York OSford University Press.

Nelson , H. ( 1963) " Ocer coming Reading Deficiencies at the college level" journal of Developmental Reading Vol.6 p.p 238.

Nuttal, C. (1982) Teaching Reading Skills Cambridge University Press.

--------- (2000). Teaching skills for in a foreign Language London Hene mann Education Books.

Perfetti , C. A (1985) Reading Ability Oxford University Press.

Sheng, H.S (2000) "A Cognitire Model for Teaching Reading Comprehension" English Teaching Fotum Vol. 38 No 4, October.

Williams , E ( 1984) Reading in the language class room London, Macmillan Publishing.

------------ ( 1990) Reading in the clas room London, Macmillan Publishing.

# አባሪ አንድ

## የፍጥነት  ንባብና የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ

**መለያ ኮድ ---------------------------------------------------------------------------**

የዚህ ፈተና አላማ የዘጠንኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት  ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡  ስለሆነም የቀረበላችሁን ምንባብ በተለመደው ፍጥነት በተመላከተ የአነባበብ ዘዴ በጥንቃቄ አንብባችሁ ስታበቁ ከምንባቡ ተንተርሰው ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች እንደየ አጠያየቅ ስልታቸው ተመርኩዛችሁ ተገቢውን  መልስ ሰጡ

## ምንባብ አንድ

### “ቀድሜ እንድበላ”

የሰው ልጅ ከፍጥረታት ሁሉ ብልህና አርቆ አሳቢ ነው፡፡ ከጥንት የጋርዮሽ ዘመን ጀምሮ የተሆያዩ ፈጠራዎችን ሲጠቀም ኖሯል፡፡ በቤቱ ውስጥ እንስሳትን እያሊመዮ ያቆያሌ፡፡ ነገርግን አንዴ ለማዲ ሳትሆን በቤት ውስጥ የምትተራመስ ጎጆዋን በሰው ጎጆ ቀሌሳ የምትኖር እንስሳን ጨርሶ ማራቅ አልቻለም፡፡ ብዙዎቹ ስሚን እንኳን ለመጥራት ሲቀፋቸው ይስተዋሊሉ፡፡ “አይጥ” በእንግሌዘኛው አጠራር mouse ወይም rat አፈጣጠሯ ከአጥቢ እንስሳት መካከል ትመደባለች፡፡ እንዱሁም በፈጣን እንቅስቃሴዋ እና በማሽተት ችልታዋ ከፍተኛነት ትታወቃለች፡፡

የአይጥ አማካኝ እዴሜ 18 ወራት ሲሆን በርካታዎቹ ግን በተለያየ ምክንያቶች አንዴ አመት ሳይሞሊቸው ይሞታለ፡፡ አይጥ በአብዛኛው በእንጨትና ከአፈር በተሰሩ ቤቶች ውስጥ በቀላሉ ገብታ ለመኖር የሚያስችሉትን ጠንካራ ጥርስም ታድላለች፡፡ አንዳንዴም በዴንጋይና በብሎኬት በተሰሩ ቤቶች ውስጥ ከገባች ዘሮቿን በማብዛት ተደላድላ ለመኖር አትቸገርም፡፡

እናም በኢትዮጵያ ደግሞ አብዛኛው ቤቶች የተሰሩት ከአፈርና ከእንጨት በመሆኑ በእያንዳንዱ ጓዳ ውስጥ አለች ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ አለቃ ገብረሃናም ምግብ በሚበለበት ቤት ውስጥ ትንሽዋ እንስሳን ከእንጀራ ማስቀመጫው መሶብ ስር በማየታቸው

"ከመሶብ አይጡ" ብለው የመረቁ መስለው ከመሶቡ ስር አይጥ ማየታቸውን አመስጥረው መናገራቸውን ታሪክ ይናገራል፡፡ ነገሩ ጥንትም ትንሿ እንስሳ እንድ ድመት ከሰዎች ጋር ተላምዳ ቤት ውስጥ እንድትኖር አይፈቀድላት እንጂ በእያንዳንዱ ቤት ጓዳ ጎድጓዳ የመገኘቷ ጉዳይ አጠራጣሪ አይደለም፡፡ ያለፈቃድ በቤት ውስጥ የመገኘቷ ጉዳይም ብዙዎችን ሲያንገበግባቸው ይኖራል፡፡

በተለይ የሰፈራችን ዕድሜ ጠገብ ልብስ ሰፊ አቶ አክሊሉ እንስሳዋን ክፉኛ አይወዳትም፡፡ በአንድ ወቅት በቤታቸው ራዲዮናቸውን ከፍተው አረፍ ባለበት ወቅት ከዘራቸው ላይ ተጠምጥማ ስታበቃ ወደ ጉድጓዶ የገባችበት ጊዜ ለእርሳቸው እንደ ህልም ነው የሚታወሳቸው፡፡ ከዚያ ጊዜ ወዲህ ላገኙት ሰው ሁሉ " ይቺ ከይሲ ፍጥረት ከዘራዬን አረከሰችው" እያሉ ለለቅሶና ለጥየቂ በሄዱባቸው ቦታዎች ሁለ ሲያንቋሽሿት ይውላሉ፡፡ " አይጥ" ብለው እንኳን ደፍረው መጥራት ስለማይሆንላቸው "ስሟን ቄስ ይጥራውና" እያሉ ነው ወጋቸውን የሚጠርቁት፡፡ እና በየእለቱ ወጥመድ ቢያዘጋጁም፣ መርዝ ቢነሰንሱ የተወሰኑትን ይገደላሉ እንጂ ጭራሽ ሊትጠፉ አልቻለችም፡፡ አዳኝ የተባሉ ድመቶችን በቤታቸው ውስጥ ቢያሰማሩም ድመቶች ከመንደር በሚቃርሙት ትርፍራፊ ሆዳቸውን ቀብድደው የቤቱ እድሜ ጠገብ ሶፋ ላይ መገልበጡን ተያይዘውታል፡፡

አንድ ቀን ታዲያ አዛውንቱ ከስራ ወደ ቤታቸው ገብተው አረፍ እንዳሉ ባለቤታቸው ምግብ ለማቅረብ መሶቡን ከፈት ቢያደርጉት አጅሪት ተስፈንጥራ ወጥታ በአልጋቸው ውስጥ ተደበቀች፡፡ አቶ አክሊሉ የዛን ቀን እህል አልበላም ብለው እስከ ምሽቱ ሶስት ሰአት ድረስ ሲግደረደሩ ቆይተው ደረቅ ዳቦ አስገዝተው ተመገቡ፡፡

አቶ አክሊሉ ነገሩ የከነከናቸው " እርሳቸው ያልበሉትን እንጀራ እንዷት አይጧ ቀድማ ትመገበዋለች" የሚለው መበለጥ ነበር፡፡ ባለቤታቸው ደግሞ " የዛሬን ነው እንዳ አይጧ ሁሌ ሽር የምትለው ከመሶብ አይደል እንዴ" ብለው ንዴታቸውን የሚያባብስ ንግግር ተናገራቸው፡፡

(ምንጭ፡- አዲስ ዘመን ጋዜጣ 77ኛ ዓመት፣ ቁጥር099፣ ሰኞ ታህሳስ 9ቀን 2010 ዓ.ም)

ስም_____________________

አፍ መፍቻ________________

I. የሚከተለትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ከልሆነ " ሀሰት" በማለት ጻፉ፡፡

1. አይጥ ከአጥቢ እንስሳት መካከል ትመደባለች፡፡

2. ከጥንት ጀምሮ አይጥ እንደ ድመት ለማዳ እንስሳ ሆና በቤት ውስጥ ትኖራለች፡፡

3. አይጥ በድንጋይና በብሎኬት በተሰራ ቤቶች ውስጥ መግባት አትችልም፡፡

4. የሰው ሌጅ ከፍጥረታት ሁለ ብሌህና አርቆ አሳቢ ቢሆንም እስከ አሁን አይጥን ከራሱ ማራቅ አልቻሉም፡፡

5. ድመቶች አይጧን መያዝ ያልቻሉት ከመንደሩ በሚቃርሙት ትርፍራፊ ሆዷቸውን ስሆሚሞለ ነው፡፡

II. የሚከተለት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለ.ኛውን መሌስ ምረጡ፡፡

6. የአይጥ አማካኝ ዕዴሜ ምን ያህሌ ነው?

ሀ. 18 ዓመት ለ. 18 ወራት ሏ. 1 ዓመት መ. 2 ዓመት

7. በኢትዮጵያ አብዛኛው ቤቶች የተሰሩት ከምንዴን ነው?

ሀ. ከብልኬት ለ. ከዴንጋይ ሏ. ከአፈርና ከእንጨት መ. ከዴንጋይና ከእንጨት

8. አቶ አክሉለ " ስሚን ቄስ ይጥራው" ያለት ማንን ነው?

ሀ. ባለቤታቸውን ለ. ከዘራቸውን ሏ. ዴመታቸውን መ. አይጧን

9. አይጥ ከፈጣን እንቅስቃሴዋ በተጨማሪ በምን ትታወቃለ.ች?

ሀ. በማሽተት ችልታዋ ከፍተኛነት ሏ. በማየት ችልታዋ ከፍተኛነት ለ.በማዴመጥ ችልታዋ ከፍተኛነት መ. በመቅመስ ችልታዋ ከፍተኛነት

10.አቶ አክሉለ እህሌ አሌበሊም ብለው እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ዴረስ የቆዩት በምን ምክኒያት ነው?

ሀ. እሳቸው ያሌበለትን እንጀራ አይጧ ቀድማ በመመገቧ ለ. ከባለቤታቸው ጋር በመጣላታቸው፡፡ ሐ. እንጀራ መብሊት ስለሌፈሇጉ መ. አይጧ አሌጋቸው ሊይ በመውጣቷ

# አባሪ ሁለት

## የፍጥነት  ንባብና የአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት

**መለያ ኮድ ---------------------------------------------------------------------------------**

**አጠቃላይ መግለጫ**

የዚህ ፈተና ዓላማ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ስለሆነም የቀረበላችሁን ምንባብ በተገቢ የአነባበብ ዘዴ አንብባችሁ ስታበቁ ከምንባቡ ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች እንደአጠያየቅ ስልታቸው መልስ ስጡ፡፡

## ምንባብ አንድ

### ስነ-ጽሑፍ

ስነ- ጽሑፍ  የሚለው ቃል በቁሙ ሲታይ በጹሁፍ የተቀረጸን የቋንቋ ጥበብ የሚመለከት ነው ፡፡ ሆኖም ስነ ጽሁፍ ከዚህ የቁም ፍቺው ባለፈ የሰውልጅ የጽሕፈት ባህል ከመጀመሩ አስቀድሞ ስሜቱን የገለጸባቸው እና ወደፊትም የሚገልጽባቸውን ቃላዊ ፈጠራዎችንም ያጠቃልላል ፡፡

በምዕራፍ ሁለት ትምህርታችን ቃላዊ የሆነውንና ያልተጻፈውን   ስነ ጽሑፍ  ስነ ቃል በሚል   ርዕስ ተመረናል ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የተጻፈውን ስነ - ጽሑፍ ምንነት እንመለከታለን ፡፡

ስለ - ስነ - ጽሑፍ ምንነት ሲነሳ ቀድሞ የሚመጣው ጥያቄ ማኛውም  የተጻፈ ነገር ሁሉ ስ' -ጽሑፍ ሊባል ይችላል ? ወይስ አይችል? የሚለው ነው ፡፡  ምላሹም ሁለት የአመለካከት አቅጣጫን የተከተለ ነው ፡፡ አንደኛው አቅጣጫ ፣ ስነ -ጽሑፍ ለመባል ዋነኛ መለኪያው በጽሑፍ ተቀርጾ መገኘቱ ነው ፡፡ ስለዚህም ደብዳቤ ፣ የእለት ማስታወሻ ፣ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ ፣ ወዘተ ሁሉ በስነ -ጽሁፍ የሚካተቱ ናቸው ››  የሚለው ሲሆን ፣ ሁለተኛው ‹‹ በጽሑፍ በሚገባ ተቀነባብሮ በቃላት የተገለጸ ሁሉ ከሱነ- ጽሑፍ የቆጠራል ማለት አይደለም ፡፡ አንድ ጽሑፍ ስነ ጽሑፋዊ ነው ለመባል መጻፉ ብቻ ሳይሆን ፣ ኪነጥበባዊ ኪነጥበባዊ ብቃት ያለው መሆን ይኖርበታል ‹‹ የሚለው አቅጣጫ ነው ፡፡ በዚህ የአመለካከት አቅጣጫ መሰረት ፣ ስነ - ጽሁፍ የሚለው ቃል በትክክል  የሚያመለክተው

የተመሰከረለት የጥራት ደረጃ ያላቸውንና ፣ በዝርው ወይም በግጥም የተጻፉ ስራዎችን ብቻ ነው ፡፡

የዚህ ምዕራፍ ትኩረት በሀለተኛው የአመለካከት አቅጣጫ ላይ የተመሰረተ ነው ፡፡ በመሆኑም ፣ ስነ - ጽሑፍ በአገላለጽ ትባቱ ፣ በህይወት ( ኑሮ ) ማሳየነቱ ፤ በሳቢነቱና የአንድ ደራሲ ወጥ ስራ በመሆኑ የተዋጣለትና ኪነጥባዊ ብቃቱ የተመሰከረለት የፈጠራ ስራ ነው ፡፡ ሰዎች ስለህይወት ያለቸውን ግንዛቤ ( የሚሰማቸውን ፣ የሚያስቡትንና የሚመኙትን ) በቋንቋ አማካይነት የሚያንጸባርቁበት ኪነጥበብ ነው ፡፡ ህይወትን ፣ እውነትንና ፈጠራን ባንድ ላይ አጣምሮ በተወሰነ ቅርጽና መጠን የሚያቀርብ በመሆኑ ውበት አለው ፣ ስሜትን ይነካል ይማርካል ፣ ያስደስታል ፡፡

ስነ ጽሑፍ ከሰው ልጅ ህይወት ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው ፡፡ የስነ -ጽሑፍ ዋነኛው ጉዳይ የሰው ልጅ ነው ፡፡ ምንጩ ፈጣሪውም ተቀባዩም ሰው ነው ፡፡ በመሆኑም ስነ - ጽሑፍ የሰው ልጅ በህይወቱ ከሚያልፍበት ውጣውረድ ይቀዳል ፤ በሰው ተፈጥሮም መልሶ ለሰው ይነገራል ፡፡ ስነ - ጽሁፍ የሰውን ጉዳይ ይዞ መልሶ ለሰው የሚቀርብ መሆኑ ደግሞ በማህበረሰብ ውስጥ ልዩ ቦታን እንዲይዝ አድርጎታል ፡፡

ለስነ - ጽሑፍ መኖር ምክንያት ናቸው የሚበሉ ሶስት ዋና ዋና ነጥቦች ይጠቀሳሉ ፡፡ የመጀመሪያው ፣ የሰው ልጅ ስለገጠመኙ ለመናገር ያለው ፍላጎት ነው ፡፡ ስው ስለ ህይወት የተገነዘበውን በጎም ሆነ ክፉ ነገር ለመስቹ ማካፈል ይፈልጋል ፡፡ ይህ ፍላጎት በሁሉም ሰዎች ዘንድ ያለና ተፈጥሮአዊ ባህሪ ቢሆንም በደራሲያን ዘንድ ያለው ግን ላቅ ያለ ነው ፡፡ ደራሲያን ከሌላው ሰው በተለየና ከፍ ባለ ደረጃ ስለ ህይወት የመናገር ፍቅር አላቸው ፡፡ ስለዚህም ህይወትን እነሱ እንደተመለከቷት ለሌላው ለማስተላለፍ ይተጋሉ ፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ፣ ደራሲያን ለሰው ልጅ ጥልቅ ፍቅርና ሰውን ለማወቅ ጽኑ - ፍላጎት ያላቸው መሆኑ ነው ፡፡ ሰዎች ምን አይነት ፍጡሮች ናቸው ? ከየት መጡ ? ወዴትስ ይሔዳሉ ባህሪዎቻቸው እንዴት ያሉ ናቸው? የአኗኗር ስርዓታቸው ምን ይመስላል? … ለነዚህና መሰል አጓጊ ጥያቄዎች እውናዊና መሳጭ መልስ ለመስጠት ይጽፋሉ ፡፡

ሶስተኛው ምክንያት ፣ የሰው ልጅ ለውበት ያለው ፍቅር ነው ፡፡ ሰው ማራኪና ሳቢነት ያለውን ነገር በአንድ ቅርጽ ተሰናድቶ ማየት ይፈልጋል ፡፡ በእውኑ ዓለም ያየውንና የሰማውን ወይም በአእምሮው የዳሰሰውን ነገር አቀነባብሮ በአንድ ቅርጽ ሲያበጀው ደግሞ ውበትን ይጎናጸፋል ፡፡ ያንን ውበት ያደንቃል ፤ ያፈቅራል ፡፡ እንዲህ ያለው የውበት

ፍቅር ደግሞ ደራሲውን እንዲፈጥር ዘውትር ይቀሰቅሰዋል ፡፡ እናም ሁል ጊዜ ይጽፋል ፡
፡

ምንጭ፡- ከቀድሞ የ9ኛ ክፍል አማርኛ ክፍል ማስተማርያ መጽሀፍ ከገጽ 34-38 የተወሰደ

**የሚከተሉትን ጥቄዎች በምንባቡ መሰረት ‹‹ እውነት ወይም ሐሰት በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለጹ ፡፡**

1. ስነ - ጽሑፍ የሚለው ቃል በቁሙ ሲታይ የሰው ልጅ ጽሕፈትን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የተገለገለባቸውን ቃላዊ ፈጠራዎች ያመለክታል ፡፡
2. አንድ ጽሑፍ ስ ጽሑፋዊ ነው ለመባል በጽሑፍ መቅረቡ ብቻ በቂ ኤደለም ፡፡
3. በጽሑፍ በሚገባ ተቀነባብሮ በቃላት የተገለጸ ሁሉ ከስ -ጽሑፍ ይቆጠራል ፡፡
4. ስነ -ጽሁፍ በማህበረሰቡ ልዩ ቦታ እንዲይዝ ያደረገው መተላለፊው በጽሑፍ መሆኑ ነው ፡፡
5. የሰው ልጅ ሁል ጊዜም ገጠመኙን ለማውጋት ያለው ፍላጎት ለስነ - ጽሑፍ መኖር እንደ

አንድ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተስማሚውን መልስ ምረጡ ፡፡

1.ከሚከተሉት አንዱ የአንድ ጽሑፍ ኪነጥበባዊ ብቃት መመዘኛ አይደለም ፡፡

ሀ.በአገላለጹ የተባ መሆን

ለ. በጽሑፍ አማካይነት መገለጽ

ሐ. ሕይወትን ማሳየት

መ. ማራኪና ሳቢ መሆን

2. ከሚከተሉት አንዱ ‹‹ የተጻፈ ነገር ሁሉ ስነ -ጽሑፍ ነው የሚሉ ወገኖችን ሀሳብ አያንጸባርቅም ፡፡

ሀ. የዕለት ውሎ ማስታወሻና የስራ ደብዳቤዎች ከስነ - ጽሑፍ ይቆጠራል ፡፡

ለ. በጽሑፍ ያልሰፈረ ነገር ስነ -ጽሑፍ ሊባል አይችልም ፡፡

ሐ. አንድ ጽሑፍ ስነ ጽሑፋዊ መሆኑ የሚረጋገጠው በጽሁፍ በመስፈሩ ነው ፡፡

መ. የአንድ ጽሑፍ ስነ ጽሑፋዊነት መለኪያው ኪነጥበባዊ ብቃቱ ነው ፡፡

3. ከሚከተሉት አንዱ ለስነ ጽሑፍ መኖር ምክንያት አየደለም

ሀ. ደራሲውን ለሰው ልጅ ያላቸው ጥልቅ ፍቅርና እሱን ለማወቅ

የሚያደረጉት ጥረት፣

ለ. የሰው ›ልጅ ገጠመኙን ለማካፈል ያለው ፍላጎት ፣

ሐ. ድርሰትን ሽጦ ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት መኖር ፣

መ. የሰው ልጅ ለውበት ጥልቅ ፍቅር ያለው መሆን ፣

4.‹‹ በጽሑፍ የተገለጸ ሁሉ ስነ - ጽሑፍ ነው ›› የሚሉ ወገኖች ለአባባላቸው ዋና መመዘኛ የሚያደርጉት ምንድ ነው

ሀ. በጽሑፍ መስፈርና አለመስፈር

ለ. በፈጠራ መንግድ መጽሐፍና አለመጽሐፍ

ሐ. ህይወትን እውነትና ፈጠራን ባንድ ላይ መያዝ አለሜዝን ፣

መ. ያልተጻፈ ስነ - ጽሑፍ መኖርን ፡

6. ‹‹ የስነ -ጽሑፍ ዋባ ጉዳይ ሰው ነው ›› ሲባል ፣ ምንን ለማመልከት ነው

ሀ. ከሰው ልጅ ገጠመኝ የሚቀዳ መሆኑን ፤

ለ. ፈባሪ ሰው መሆኑን ፣

ሐ. የሚጻፈው ለሰው መሆኑን ፣

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

## አባሪ ሶስት

## የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድና ሁለት ዝርዝር መረጃ

## የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎች

## ከ10%

| ከመለያ ኮድ | ፈተና አንድ | ፈተና ሁለት | አማካይ |
|---|---|---|---|
| 1 | 9 | 6 | 7.5 |
| 2 | 7 | 8 | 7.5 |
| 3 | 6 | 5 | 5.5 |
| 4 | 5 | 7 | 6 |
| 5 | 6 | 10 | 8 |
| 6 | 4 | 3 | 3.5 |
| 7 | 8 | 9 | 8.5 |
| 8 | 6 | 5 | 5.5 |
| 9 | 4 | 4 | 4 |
| 10 | 4 | 4 | 4 |
| 11 | 9 | 8 | 8.5 |
| 12 | 7 | 6 | 6.5 |
| 13 | 3 | 2 | 2.5 |
| 14 | 7 | 8 | 7.5 |
| 15 | 5 | 7 | 6 |
| 16 | 9 | 7 | 8 |
| 17 | 3 | 5 | 4 |
| 18 | 8 | 10 | 9 |
| 19 | 4 | 4 | 4 |
| 20 | 5 | 2 | 3.5 |
| 21 | 6 | 9 | 7.5 |
| 22 | 4 | 6 | 5 |
| 23 | 7 | 5 | 6 |
| 24 | 6 | 3 | 4.5 |
| 25 | 8 | 5 | 6.5 |
| 26 | 7 | 10 | 8.5 |
| 27 | 7 | 5 | 6 |
| 28 | 8 | 8 | 8 |
| 29 | 6 | 5 | 5.5 |
| 30 | 7 | 8 | 7.5 |
| 31 | 4 | 3 | 3.5 |
| 32 | 4 | 6 | 5 |

| ከመለያ ኮድ | ፈተና አንድ | ፈተና ሁለት | አማካይ |
|---|---|---|---|
| 33 | 9 | 7 | 8 |
| 34 | 5 | 6 | 5.5 |
| 35 | 3 | 7 | 5 |
| 36 | 5 | 3 | 4 |
| 37 | 6 | 9 | 7.5 |
| 38 | 4 | 2 | 3 |
| 39 | 7 | 9 | 8 |
| 40 | 9 | 5 | 7 |
| 41 | 2 | 5 | 3.5 |
| 42 | 4 | 8 | 6 |
| 43 | 3 | 4 | 3.5 |
| 44 | 8 | 6 | 7 |
| 45 | 4 | 8 | 6 |
| 46 | 2 | 3 | 2.6 |
| 47 | 6 | 9 | 7.5 |
| 48 | 4 | 6 | 5 |
| 49 | 5 | 2 | 3.5 |
| 50 | 8 | 10 | 9 |
| 51 | 3 | 5 | 4 |
| 52 | 4 | 7 | 5.5 |
| 53 | 4 | 6 | 5 |
| 54 | 10 | 9 | 9.5 |
| 55 | 2 | 4 | 3 |
| 56 | 4 | 5 | 4.5 |
| 57 | 8 | 7 | 7.5 |
| 58 | 7 | 5 | 6 |
| 59 | 5 | 3 | 4 |
| 60 | 7 | 10 | 8.5 |
| 61 | 10 | 9 | 9.5 |
| 62 | 4 | 5 | 4.5 |
| 63 | 4 | 6 | 5 |
| 64 | 5 | 7 | 6 |
| 65 | 4 | 6 | 5 |
| 67 | 3 | 7 | 5 |
| 68 | 4 | 5 | 4.5 |
| 69 | 6 | 8 | 7 |
| 70 | 2 | 7 | 4.5 |
| 71 | 7 | 7 | 9 |
| 72 | 2 | 5 | 7 |
| 73 | 10 | 8 | 3.5 |
| 74 | 6 | 8 | 9 |

| ከመለያ ኮድ | ፈተና አንድ | ፈተና ሁለት | አማካይ |
|---|---|---|---|
| 75 | 4 | 4 | 7 |
| 76 | 7 | 10 | 4 |
| 77 | 4 | 5 | 8.5 |
| 78 | 5 | 6 | 4.5 |
| 79 | 5 | 3 | 5.5 |
| 80 | 8 | 6 | 4 |
| 81 | 9 | 7 | 7 |
| 82 | 6 | 6 | 8 |
| 83 | 7 | 4 | 6 |
| 84 | 8 | 9 | 5.5 |
| 85 | 9 | 9 | 8.5 |
| 86 | 6 | 6 | 9 |
| 87 | 5 | 2 | 3.5 |
| 88 | 10 | 8 | 9 |
| 89 | 3 | 3 | 3 |
| 90 | 5 | 6 | 5.5 |
| 91 | 7 | 9 | 8 |
| 92 | 3 | 5 | 4 |
| 93 | 7 | 5 | 6 |
| 94 | 4 | 4 | 4 |
| 95 | 8 | 10 | 9 |
| 96 | 9 | 8 | 8.5 |
| 07 | 5 | 5 | 5 |
| 08 | 10 | 7 | 8.5 |
| 99 | 6 | 4 | 5 |
| 100 | 8 | 5 | 6.5 |
| | ድምር 585<br>5.85<br>ልይይት 4.620636<br>መ/ልይይት<br>2.149564208 | 617<br>6.17 አማካይ<br>ልይይት 5.146262<br>መደበኛ ልይይት<br>2.2695237 | 601<br>60.1<br>ልይይት 4.883413<br>መ/ልይይት<br>2.209844 |

# አባሪ አራት

## የንባብ ፍጥነት አንድና ፈተና ሁለት ዝርዝር መረጃ

| የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተናዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መለያ ኮድ | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ፈተና 1 ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሰኮንድ | ፈተና 1 ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሰኮንድ | አማካይበሴኮንድ |
| 1 | ሸክኛ | 175 | 280 | 237.5 |
| 2 | “ | 243 | 280 | 261.5 |
| 3 | “ | 376 | 319 | 347.5 |
| 4 | “ | 295 | 319 | 307 |
| 5 | “ | 265 | 235 | 250 |
| 6 | “ | 390 | 319 | 354.5 |
| 7 | “ | 230 | 179 | 204.5 |
| 8 | “ | 334 | 280 | 307 |
| 9 | “ | 334 | 406 | 370 |
| 10 | “ | 334 | 302 | 318 |
| 11 | “ | 175 | 203 | 189 |
| 12 | “ | 265 | 263 | 264 |
| 13 | “ | 414 | 447 | 430.5 |
| 14 | “ | 175 | 280 | 237.5 |
| 15 | “ | 295 | 235 | 265 |
| 16 | “ | 230 | 179 | 204.5 |
| 17 | “ | 334 | 302 | 318 |
| 18 | “ | 175 | 263 | 219 |
| 19 | “ | 334 | 447 | 390.5 |
| 20 | “ | 356 | 406 | 381 |
| 21 | “ | 243 | 235 | 239 |
| 22 | “ | 295 | 302 | 298.5 |
| 23 | “ | 295 | 263 | 270 |
| 24 | “ | 334 | 319 | 326.5 |
| 25 | “ | 295 | 263 | 279 |
| 26 | “ | 202 | 203 | 202.5 |
| 27 | “ | 295 | 280 | 287.5 |
| 28 | “ | 202 | 160 | 181 |
| 29 | “ | 395 | 319 | 307 |
| 30 | “ | 265 | 263 | 264 |
| 31 | “ | 334 | 319 | 326.5 |
| 32 | “ | 334 | 319 | 326.5 |
| 33 | “ | 202 | 203 | 202.5 |
| 34 | “ | 334 | 280 | 307 |

| መለያ ኮድ | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ፈተና 1 ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሰኮንድ | ፈተና 1 ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሰኮንድ | አማካይበሴኮንድ |
|---|---|---|---|---|
| 35 | ሽክኛ | 334 | 280 | 307 |
| 36 | “ | 334 | 406 | 370 |
| 37 | “ | 295 | 280 | 287.5 |
| 38 | “ | 356 | 302 | 329 |
| 39 | “ | 175 | 105 | 170 |
| 40 | “ | 265 | 263 | 264 |
| 41 | “ | 356 | 302 | 329 |
| 42 | “ | 295 | 280 | 287.5 |
| 43 | “ | 356 | 406 | 381 |
| 44 | “ | 265 | 280 | 272.5 |
| 45 | “ | 295 | 280 | 287.5 |
| 46 | “ | 414 | 447 | 430.5 |
| 47 | “ | 265 | 203 | 234 |
| 48 | “ | 295 | 280 | 287.5 |
| 49 | “ | 175 | 302 | 329 |
| 50 | “ | 414 | 160 | 167.5 |
| 51 | “ | 265 | 447 | 430.5 |
| 52 | “ | 295 | 263 | 279 |
| 53 | “ | 334 | 280 | 307 |
| 54 | “ | 175 | 165 | 170 |
| 55 | “ | 414 | 447 | 430.5 |
| 56 | “ | 334 | 319 | 326.5 |
| 57 | “ | 243 | 179 | 211 |
| 58 | “ | 265 | 280 | 272.5 |
| 59 | “ | 365 | 406 | 318 |
| 60 | “ | 265 | 203 | 234 |
| 61 | “ | 202 | 179 | 190.5 |
| 62 | “ | 356 | 280 | 318 |
| 63 | “ | 295 | 280 | 289.5 |
| 64 | “ | 265 | 263 | 264 |
| 65 | “ | 295 | 302 | 298.5 |
| 66 | “ | 175 | 165 | 170 |
| 67 | “ | 365 | 319 | 337.5 |
| 68 | “ | 295 | 302 | 329 |
| 69 | “ | 356 | 280 | 287.5 |
| 70 | “ | 295 | 302 | 329 |
| 71 | “ | 356 | 263 | 264 |
| 72 | “ | 265 | 406 | 381 |
| መለያ ኮድ | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ፈተና 1 ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሰኮንድ | ፈተና 1 ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሰኮንድ | አማካይበሴኮንድ |
| 73 | ሽክኛ | 175 | 179 | 177 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 74 | “ | 295 | 235 | 265 |
| 75 | “ | 356 | 406 | 381 |
| 76 | “ | 243 | 280 | 261.5 |
| 77 | “ | 334 | 319 | 326.5 |
| 78 | “ | 295 | 263 | 279 |
| 79 | “ | 334 | 302 | 318 |
| 80 | “ | 258 | 203 | 230.5 |
| 81 | “ | 230 | 179 | 204.5 |
| 82 | “ | 295 | 319 | 307 |
| 83 | “ | 295 | 285 | 265 |
| 84 | “ | 175 | 160 | 167.5 |
| 85 | “ | 280 | 179 | 204.5 |
| 86 | “ | 334 | 235 | 284.5 |
| 87 | “ | 356 | 406 | 281 |
| 88 | “ | 202 | 160 | 181 |
| 89 | “ | 414 | 447 | 430.5 |
| 90 | “ | 295 | 319 | 307 |
| 91 | “ | 243 | 165 | 203 |
| 92 | “ | 365 | 280 | 318 |
| 93 | “ | 265 | 302 | 283.5 |
| 94 | “ | 365 | 319 | 337.5 |
| 95 | “ | 202 | 165 | 183.5 |
| 96 | “ | 202 | 179 | 190.5 |
| 97 | “ | 334 | 406 | 370 |
| 98 | “ | 202 | 179 | 190 |
| 99 | “ | 334 | 319 | 326.5 |
| 100 | “ | 265 | 280 | 272.5 |
| | | 29027<br>**አማካኝ**<br>290.27<br>0.0713129 | 28058<br>**አማካይ**<br>280.58<br>0.079763 | 28542.5<br>2.85.42<br>0.0754664 |

## አባሪ አምስት

### ቃል መጠይቅ ለመምህራን

### በ2016 ዓ.ም. በኩቢጦ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እያስተማሩ ከሚገኙ መምህራን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

## ዝርዝር ጥያቄዎች

1. በአጠቃላይ ሲታይ 9ኛ ክፍል አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል ብለው ይላሉ?
2. ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ችግር አለባቸው የሚሉ ከሆነ ችግሩ ከምን የመነጨ ይመስልዎታል?
3. በየሚያስተምሩባቸው ክፍሎች የሚገኙ ፈጣንና ዝግተኛ የሆኑ ተማሪዎችን በውል ለይተው ያውቋቸዋል?
4. ከሙያዎ ልምድ በመነሳት ከፈጣንና ከዝግተኛ አንባቢዎች የትኞቹ የተሸለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው ይላሉ?
5. ተማሪዎች በየክፍለ ጊዜም ሲያስተምሯችው የንባብ ልምምድ የሚያደርጉት እንዴት ባለ ዘዴ ተጠቅመው ነው
6. ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው ብለው ይላሉ
7. በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማወቅ በግል ወይም በቡድን በመሆን በትምህርት ቤት ደረጃ የተሰሩ ጥናታዊ ስራዎች አሉ? ካሉስ ያስገኙትን ውጤት እንደት ይገልፁታል

----------------------------------------------------------------------------------------------------

8. የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ለማዳበር ምን ቢደረግ ይሻላል ይላሉ
9. የንባብ ትምህርትን ለማዳበር የሚቻለው በቋንቋ መ/ራን ላይ ብቻ ሳንወሰን የተለያዩ የትም/ት አይነቶች በሚያስተምሩ መ/ራን የጋራ ጥረትና ርብርቦሽ ነው ቢባል በተሰነዘረው ሀሳብ ይሰማማሉ
10. የተማሪዎችን የንባብ ችግር ለመቅረፍ ከየተማሪው ወላጆች ጋር ተገናኝቶ በመወያየት በኩል ምን ያህል ተጉዘዋል
11. በመጨረሻ ተጨማሪ አስተያየት ካፈዊት ይግለፁ

## ለመምህራን ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ
## መምህር አንድ

**ጥያቄ**

1 በአጠቃላይ ሲታይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?

**መልስ**

በየማስተምርባቸው ክፍሎች በጥቂት ቁጥር መገለፅ ከሚችሉ ተማሪዎች በስተቀር በአጠቃላይ ማት በሚቻል መልኩ ከፍተኛ የሆነ የንባብ ችግር አለባቸው እንኳን አንብቦ መረዳት ይቅርና ፊደልን የማይለዩ ተማሪዎች አሉ፡፡ ለዚህም ፊደላትን መለየት ካለመቻላቸው የተነሳ የራሳቸውን መጠሪያ ስም ሲፅፉም ግድፈት አለባቸው.. እዚህ ላይ ችግሩ የኔ ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር አቀፍ የጎላ ችግር እንደሆነ አምናለሁ፡፡

**ጥያቄ**

2 ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ችግር አለባቸው የሚሉ ከሆነ ችግሩ ከምን የመነጨ ይመስልዎታል?

**መልስ**

ተማሪዎች በቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት ላይ ችግሩን ቀርፊው መምጣት በሚያስችላቸው መልክ አልተሰራም፡፡ ስለዚህ በምክንያትነት የምጠቅሰው ስንከተለው በነበረው የትምህርት ፖሊሲ ተጠቃሽ ሲሆን ከ1ኛ -4ኛ ክፍል በአንድ መምህር ሁሉንም ትምህርት እንዲማሩና ሳይወድቁ ከክፍል ወደ ክፍል እየተሸጋገሩ እንዲመጡ መደረጉ ዋነኛ ችግር ነው፡፡ ሌለው በየክፍሉ የሚመደቡ መ/ራ የግል ብቃት ከግምት አለመግባቱ የደካማው መ/ር ተማሪዎች ምንም ሳይጨበጡ እንዲዘልቁ አድርጓቸዋል፡፡ ብዬ እገምታለሁ፡፡ ሌላው መጠቀስ ያለበት ኢ-አፊፊት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ጥላቻና መጥፍ አመልካከት ይዘው እንዲያድገ መደረጉ ቋንቋውን ለማወቅ ያላቸው ተነሳሽነት አነስተኛ እንደሆነ እረዳለሁ፡፡ በመጨረሻ የማክለው ሃሳብ ቢኖር አማርኛ

ቋንቋ በሁለተና ደረጃ መልቀቂ ብሔራዊ ፈተና ላይ አለመሰጠቱ ምንያደርገልኛል የሚል አመለካከት በውስጣቸው እንዲጎለብት አድርጓል እላለሁ፡፡

ጥያቄ

3 በሚያስተምሯቸው ክፍሎች የሚገኙ ፈጣንና ዝግተኛ የሆኑ ተማሪዎችን በወል ለይተው ያውቋቸዋል?

መልስ

በየክፍለ ጊዜዬ ገብቶ ከማስተማር በስተቀር ሁኔታውን ልብ አላልኩም ሆኖም በየክፍለጊዜው በተማሪዎች መነበብ ያለባቸውን ምንባቦች እያደረሰኩ ለማሳነበብ በማደርገው ጥረት በጣም ጥቂቶች በተሻለ ሁኔታ ሲያነቡና ሲረዱ አብዛኛዎቹ ተነስተው ለማንበብ ባለመቻላቸው ሰቢያ ፈቀደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ አስተውያለሁ ያይህ ማለት በማንበብ ላይ የማይሳተፉት ተማሪዎች ዝግተኛ አንባቢዎች እንደሆኑ እረዳለሁ፡፡ ሆኖም በጥናት ላይ የታገዘ ሥራ አለክናወንኩም፡፡

ጥያቄ

4 ከሙያዎ ልምድ በመነሳት ከፈጣንና ከዝግተኛ አንባቢዎች የትኞቹ የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው ይላሉ?

መልስ

ፈጣን አንባዎች ከዝግተኛ አንባቢዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው ምክንያቱም ፈጣን አንባቢዎች ከሞላ ጎደል ፊደላቱን ሳይገድፉ ስለሚያነቡ የምንባቡን መልዕክት ከወዲሁ በአዕምሮአቸው ቀርጸ የማስቀረትና የመረዳት ብቃቱ አላቸው፡፡

ጥያቄ

5 ተማሪዎችዎን ሲያስተምሯቸው የንባብ ልምምድ የሚያደርጉት እንዴት ባለ ዘዴ ተጠቅመው ነው?

መልስ

ተማሪወች በቡድን ተጣምረው እንዲሰሩ ፍላጎት ስላለኝ ኢ-አፍፈት ተማሪዎችን ከአፍ ፈት ተማሪዎች ጋር በቡድን አጣምሬ እንደሰሩ ለማድረግ ቡድን የመሰረት ሲሆን ምንባቡ በየቡድናቸው እንዲያነቡና እንዲወያዩበት አስቀድሜ አደርጋለሁ፡፡

ከዚያ ከቡድናቸው በዕለቱ አንድ ቡድን ሊሆን ይችላል ተነስቶ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲያነብ አደርጋለሁ ሲያነብ እየተከታተልኩ ግድፈቱን እያረመ እንዲሄድ አድርጋለሁ በመጨረሻም ምንባቡን ለተማሪዎች አነብና ሳበቃ የምንባቡን መልዕክት ለየቡድኑ እድሉን በመስጠት እንዲገልፁ አደርጋለሁ፡፡ ቡድን በዚህ መልክ ያዋቀርኩበት ምክንያት አ-አፍፊት ተማሪዎች ከተማሪዎች ጋር ሲሆኑ ሀሳባቸውን በሚችሉት የቋንቋ መጠን ልክ ያለፍራቻ መግለፅ ይችላሉ ብዬ ስለማስብ ነው፡፡

**ጥያቄ**

6 ተማሪዎች አንብበው የመረዳት ችሎታውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ሙሉ በሙሉ ማለት ሚያስችል በሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው ብለው ይላሉ?

**መልስ**

በተማሪዎች በኩል ሙሉ በሙሉ ማለት በሚያስችል መልኩ የንባብ ፍጥነቱንም ሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታውን የተሸለ ደረጃ ለማድረስ ጥረት ሲደረግ አይታይም ከመምህራኑም በኩል ከተለያዩ ምንባቦች ጋር እራሳቸውን እንዲያገናኙ ግፊት አይታይም፡፡

7 የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማወቅ በግል/ በቡድን / በመሆን የተሰሩ ስራዎች አሉ

**መልስ**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከዞን ትምህርት ቢሮ ከተሰጠ ስልጠና በኋላ የንባብ ችግር ስር ሰደደ መሆኑ ከታመነበት በኋላ ከስብሰባው ባገኘሁት መጠነኛ ግንዛቤ በመጠቀም የተማሪዎችን ንባብ ፍጥነት በመጠኑ ለመለካት ምክሬ ነበር በዚህም ፈጣን አንባቢዎች በደቂቃ እስከ 115 ቃላትን ሲያነቡ ያሳተፍኳቸው ሌሎች ሁለት ተማሪዎች በደቂቃ ከ55-60 ቃላትን ማንበብ መቻላቸውን ለማየት ችያለሁ፡፡ ሆኖም ዘለቄታዊ መፍትሄ ሊያመጣ በሚችል መልኩ አልሄድኩበትም እንደ ትምህርት ቤትም ቀደሞ የተሰራ ስራ አላየሁም በዚህ፡፡ ቃለ መጠይቅ ላይ ያሳተፈኝ ጥናት አድራጊ መ/ር የመጀመሪያ ነው ብል አልተሳሳትኩም

ጥያቄ

8 የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ለማዳበር ምን ቢደርግ ይሻላል ይላሉ?

መልስ

እንደግ አስተያየቴ ማለት የምፈልገው አስቀድሞ በት/ቤቱ አብዛኛውን ተማሪ ኢ-አፍፊት ተማሪ በመሆኑ ከልጅነቱ ጀምሮ ስለ አማርኛ ቋንቋ እንዲይዝ የተደረገው ጥላቻና መጥፎ አመልካከት የሚወገድበት መንገድ እንደመንግስትና እንደክልል ቢሰራበት ጥሩ ነው እላለሁ፡፡ ሌላው በሳምንት ያለው ክ/ጊዜ በላምንት አንድ ብቻ መሆኑ ቢስተካከል ከወላጅ ጋር ቅርብ የሆነ ግንኙነት በመፍጠር ችግሩ የሚቀርፍበትን መንገድ ማመቻቸት ቋንቋ ትምህርቱ በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ላይ መስጠት ቢችል ትኩረት ሊያገኝ ይችላል መምህራንም መምከርና የተሻሉ ሁኔታዎች ማመቻቸት አለባቸው፡፡

ጥያቄ

9 የንባብ ትምህርትን ለማዳበር የሚቻለው በቋንቋ መ/ራን ላይ ብቻ ሳንወሰን የተለያየ የትምህርት አይነቶችን በሚያስተምሩ መ/ራን የጋራ ጥረትና ርብርቦሽ ነው ቢባል በተሰነዘረው ሀሳብ ይስማማሉ?

መልስ

አዎ ጥሩ ጥያቄ ነው የቀረብክልኝ ሁሉም የትህርት አይነቶች የሚቀርቡት በቋንቋ አማካይነት በመሆኑ የሂሳብ ትምህርቱንም ሆነ ሌለች የትምህርት ኤነቶች ተበተገቢው ለመስራት መረዳት አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም ትኩረት ሰጥተው ሊረባረቡበት ይገባል፡፡ ይህ ማለት የማንናውም የትምህርት አይነት ውስጣዊ መልዕክት ያለ አንብቦ መረዳት ትርጉም የልጅ ነው፡፡

ጥያቄ

10 የተማሪዎችን የንባብ ችግር ለመቅረፍ ከተማሪ ወላጅ ጋር ትገኛኝቶ በመወያየት በኩል ምን ያህል ተጉዘዋል?

**መልስ**

በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ወላጆቻቸው በገጠር ገበሬ ማህበራት ርቀው ያሉ በመሆናቸው አጥጋቢ የሆነ ስራ ስሪቻለሁ ማለት አልደፍርም ሆኖም በከተማ ከሚገኙ ወላጆች ጋር በልጆቻቸው ዙሪያ ለመነጋገር ሲያስፈልግ በማስጠራት ልጆቻቸው የቤት ስራ ሰርተው እንደማይመጡ በንባብም ሆነ በትምህርት ደካማ መሆኑናቸውን፣ በማሳወቅ በቤት በኩል እገዛና ቁጥጥር እንዲደያደርጉላቸው እገልፃለሁ፡፡

**ጥያቄ**

11 ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት ግለፁ

- በተለይ ንባብን በተመለከቱ እንደ ሀገር አሳሳቢ የሆነ ደረጃ ላይ ደርሰናል ብል አልተሳሳትኩም ሁሉም ያገባኛል ባይ አካላት ትከኩረት ሰጥተውበት የችግሩን በጥናትለይቶ በማውጣት ወደተሸለ ሁኔታ እንድንመጣ በየጊዜው ትምህርት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ቢሰጥ የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

## መምህር ሁለት

ጥያቄ

1. በአጠቃላይ ሲታይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል ይላሉ?

መልስ

አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ በተለይ ኢአፍፊት ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ ሲጠየቁም ፈቃደኛነት አይታይባቸውም ችግሩ እንደ ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን እንደ ሃገር አቀፍ አሳፊሪ የሆነ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ብል አልተሳሳትኩም ተማሪው በውስጡ ምን እንደሚያስብ በውል ባልረዳም ፊፅሞ ፍላጎትና ተነሳሽነት አይታይበትም፡፡

ጥያቄ

2. ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው የሚሉ ከሆነ ይህ ችግር ከምን መነጨ ይመስልዎታል?

መልስ

ስንከተለው ነበረው የትምህርት ፖሊሲ ለተማሪዎች እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ በዋነኛነት ተጠቃሽ ነው፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ እኩል የሆነ አንብቦ የመረዳት

ችሎታና ማንበብ ብቃት አለመኖሩ ወጥነት ባለው የክፍል ደረጃ ላይ ፊደላቱን መማር እንዲጀምሩ አለመደረጉ አንድ ምክንያት ይመስለኛል፡፡ ሌላው ወደ ሁለተኛ ደረጃ ከመምጣታቸው በፊት አንደኛ ደረጃ ላይ የነበሩት ጊዜ አወቁም አላወቁም ከክፍል ወደ ክፍል እየተሸጋገሩ እንዲመጡ መደረጉ ምክንያት ነው ብዬ እላለሁ፡፡

**ጥያቄ**

3. በሚያስተምሯቸው ክፍሎች የሚገኙ ፈጣንና ዝግተኛ የሆኑ ተማሪዎች በውል ለይተው ያውቃቸዋል?

መልስ

ፈጣንና ዝግተኛ የሆኑ ተማሪዎች በውል ለይቼ ለማወቅ ያደረግሁት ጥረት የለም ምክንያቱም በሳምንት ለየክፍሉ የተመደበ የክፍል ጊዜ ብዛት አንድ ብቻ በመሆኑ ተማሪዎቹን ለይቼ እንድረዳ ሊደርገኝ አልቻለም ሆኖም እኔም ቋንቋ ተማሪ እንደመሆኔ መጠን ፈጣን አንባቢዎች በዝግተኛ አንባቢዎች የተሸለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳላቸው አምናለሁ፡፡

**ጥያቄ**

4. ከሙያዊ ልምድ በመነሳት ከፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎች የትኞቹ የተሸለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው

**መልስ**

ከላይ እንደገልፅኩት ፈጣን አንባቢዎች ከዝግተኛ አንባቢዎች የተሸለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው

**ጥያቄ**

5. ተማሪዎችን በየክፍለ ጊዜዎ ሲያስተምሯቸው የንባብ ለምምድ የሚያደርጉት እንዴት ያለ ዘዴ ተጠቅመው ነው?

**መልስ**

ክፊለ ጊዜው በሳምንት ለአንድ ክፍል አንድ ብቻ  ስለሆነ የዕለቱ ትምህርት በምንባብ ላይ የሚያተኩር ከሆነ ክፍለ ጊዜውን ለማብቃቃት በቅድሚያ አንድ

ወይም ሁለት ተማሪዎች ቆመው እንዲያነቡ ዕድል እስጣለሁ ተማሪዎቹም እንዲያደምጡ  አድጋለሁ ተማሪዎቹ ምንባቡን ሲገድፉ እርማት በመስጠት እንዲያስተካክሉ አድርጌ በመጨረሻ ምንባቡን እኔው አነብላቸውና የምንበቡ መልዕክት በምን ላይ እንደተከረ በጋራ ውይይተ ታግዘን መልዕክቱን እንዲረዱት አደርጋለሁ፡፡

ጥያቄ

6. ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የንባብ ፍጥነታቸውን ለማደበና የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው ብለው ይላሉ?

መልስ

የሚያደርጉት ጥረት፣ ፍላጎትና ተነሳሽነት ፈፅሞ አይታዎኝም እንኳን ሌሎች መፃህፍት ሊየነቡ አይደለም ከቀረበላቸው መንባብ ላይ የወጡ የመልመጃዎች ጥያቄዎች ሠርተው እንዲመጡ ሲታዘዙ ከውስን ተማሪዎች በስተቀር ሠርተው ሲመጡ አይታይም ይህም  የሚያሳየን የንባብ ልምዶቸውም ሆነ ፍጥነታቸው አነስተኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ነው፡፡

ጥያቄ

7. የተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማወቅ በግል ወይም በቡድን በመሆን በትምህርት ቤት ደረጃ የተሰሩ ጥናታዊ ስራዎች አሉ?  ካሉስያስገኙት ውጤት እንዴት ይገለፃል?

መልስ

በየምዕራፉየቀረቡ ምንባቦችን በግልም ሆነ በቡድን እንዲያነቡ በማድረግ ከየምንባቡ ስር የቀረቡ መልመጃዎችን እንደሰሩ በማድረግ ከሚደረገው መለካት በስተቀር ምንም የተሰራ ስራ በግልም ሆነ በቡድን አላየሁም የሙያዬ ባልደረባ በዚህ ጥናት የሚያገኘውግኝት ለኔም ለትምህርት ቤቱም ፈር ቀዳጅ ይሆናል ብዬ አስባለሁ

ጥያቄ

8. የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ለማዳበር ምን ቢደረግ ይሻላል ይላሉ?

መልስ

መልስ ህፃናት የንባብ ልምዳቸውን ሚያዳብሩት ከቤት ጀምረው ስለሆነ ለወላጆች ግንዘበ በማስጨበጥ ህፃናትና መጻህፍት እንዲተዋወቁ ቢደረግ ሥርዓተ ትምህርቱ በየጊዜው እየተፈሸ መሂድ ቢችል ለመምህራን በማስተማር ሥነ ዘዴ ዙሪያ ላ ተከታታይ ስልጠና የሚሰጥበት ሁኔታ ቢመቻች ሌላው ፊደላትን በውስጥ ያለይ ህፃናት ተማሪዎችን ከክፍል ወደ ክፍል እንዲሸጋገሩ የሚያደርጉ ሁኔታ እርማት ቢወሰድበት ጥሩ ነው እላለሁ፡፡ በተጨማሪ ወላጅ ትምህርት ቤትና መምህር መካከል ጥብቅ የሆነ ግንኙነት ሊኖር ይገባል ብዬ እንደገል አምናለሁ፡፡

ጥያቄ

9. የንባብ ትምህርት ለማዳበር የሚቻለው በቋንቋ መ/ራን ላይ ብቻ ሳንወሰን የተለያየ የትምህርት አይነቶችብ በሚያስተምሩ መ/ራን የጋራ ጥረትና ርብርቦሽ ነው ቢባል በተስነዘረው ሀሳብ ይስማማሉ?

መልስ

አዎ እሰማማለሁ የንባብ ችግርየቋንቋ መምህራን ብቻ ችግር አይደለም፡፡ በነሱም ብቻ የሚፈታ አይደለም፡፡ ሁሉም የትምህርት አይነቶች ያለቋንቋ ሊተላለፉ አይችሉም፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የራሳቸው የሆነ አካሄድና ትዕዛዝ አላቸው እንዲሁም በውስጣቸው የያዙትም ሀሳብ በጽሁፍ ተቀናብሮ የቀርበ በመሆኑ የያዙትውስጣዊ ሃሳብ የሚገለፀውና መረዳት የሚቻለው በምንባብ አማካይነት ስለሆነ ሁሉም ሙያተኛ ሌሎችም አካላት ትኩረት ሊሰጡት ይገባል

ጥያቄ

10. የተማሪዎችን የንባብ ችግር ለመቅረፍ ከተማሪ ወላጆች ጋር ተገናኝቶ በመወያየት በኩል ምን ያህ ተጉዘዋል

መልስ

አስቤበት ሳይሆን አጋጣሚ በተማሪው በሚፈጠር የቤት ስራ አለመስራት ከትምህርት ቤት ያላግባብ መቅረትና በፈተናዎች ላይ አለመገኘት በመሳሰሉ ጉዳዮችወላጅ እንዲያመጡ አዥገቬ ከወላጅ ጋር ከማደርገው ውይይት ውጭ በተሰጠው ነጥብ ላይ

በትኩረት አልሰራሁበትም፡፡ ተማሪው የማንበብ ችግር እንዳለበት ግን ሳልጠቁም አላልፍም፣

ጥያቄ

11.ተጨማሪ አስተያየት ካለዎች ገለፁ?

- ከላይ በሌሎችና በኔም የተጠቀሱት አስተያየቶች ተፈትሸው ስራ ላይ የሚውሉበት ሁኔታ በመቻች የማይቀረፉ ችግር ስለማኖር የተሸለ ሁኔታ ፈጠራል የሚል እምነት አለኝ

## መምህር ሦስት

ጥያቄ

1. በአጠቃላይ ሲታ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ ገኛል ብለው ይላሉ?

መልስ

ምንባብ በተገቢው አንብቦ መረዳት አይችሉም ማለት በመማር ላይ ያሏቸውን የተለያዩ የትምህርት አይነቶች መረዳት አይችሉም ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ እንደ አገርም አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ያለን መሆናችን ያሳያል እኔም ቋንቋ መምህር እንደመሆኔ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲበዛ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለመሆኑን ተረድቼአለሁ፡፡

ጥያቄ

2. ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው የሚሉ ከሆኑ ችግሩ ከምን የመነጨ ይመስልዎታል፡፡

መልስ

በቅድሚያ ከጅምሩ ተማሪዎች ወደ ት/ቤት አለም ሲደባለቁ በተገቢ ሁኔታ የቋንቋውን የፊደል ዝርያዎች ሳይለዩ ሆሄ አጋጣጥመው ቃላትን መመስረትና ማንበብ ሳይችሉ ከክፍል ወደ ክፍል እየተሸጋገሩ እንደመጡ መደረጉ በየክፍሉ የተመደቡላቸው መምህራን የቋንቋ ብቃትን የማስተማር ሥነ ዘዴ ሳይታይ እንዲማሩ መደረጉና መምህሩም ከሚደርስበት የግምገማ ውርጅብኝ ላይ መውደቅ የሚገባቸውንም እያሳለፉ ለተከተይ ክፍል እንዲበቁ ማድረጉ በክፍል ውስጥ የተማሪው ቁጥር መብዛትና ተገቢ ክትትል ለማድረግ አለመቻል የመሳሰሉትን ምክንያት ይሆናሉ እላለሁ፡፡

ጥያቄ

3. በሚያስተምሩት ክፍሎች ሚገኙ ፈጣንና ዝግተኛ የሆኑ ተማሪዎችን በውል ሌተው ያውቃሉ?

መልስ

በሁለቱ መካከል ያለውን ለመለየት ያደረግኩት ጥናት ወይም የተለየ ስራ የለም፡፡ ሆኖም የተሸለ የማንበብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚያሳዩት ተሳትፎና አረዳድ አኳያ ፈጣን ተማሪዎች ከዝግተኛ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት አቅም ያላቸው መሆኑን አምናለሁ፡፡

ጥያቄ

4. ከፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎች የተሸለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው?

መልስ

ፈጣን አንባቢዎች በተሸለ ሁኔታ አንብቦ የመረዳት አቅም አላቸው

ጥየቄ

5. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍል ጊዜ የንባብ ልምምድ የሚያደርጉ እንዴት ባለ ዘዴ ነው?

መልስ

በማስተምርባቸው ክፍሎች ተማሪዎች እንደብቃታቸው በማዳባለቅ ያደራጀዋቸው ስለሆነ በቅድሚያ ምንበቡን በለሆሳስ በቡድን ሆነው እንዲያነቡ አደርጋለሁ ምክንያቱም አንብቦ ለመረዳት ይህ ዘዬ ተመራጭ መሆኑን ስለማምን ዘዴው እንዲታገበር አደርጋለሁ፡፡ ከዚያም ከየቡድኑ ተነስተው በንባብ እንዲያሰሙ በማድረግ በንባብ ያሳዩትን ግድፈቶች እርማት በመስጠት በመጨረሻ ላይ እራሴ አንብቤላቸው ሳበቃ ከወይይቱ ያገኙትን ሀሳብ እንዲገለፁ በማድረግ የራሴን ሀሳብ አክዬ ግንዛቤ እንዲጨበጡ አደርጋለሁ

ጥያቄ

6. ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው ብለው ያምናሉ?

መልስ

ይህነው የሚባል ጥረት ሲያደርጉ አይስተዋልም ፡፡ ከራሳቸው የመማሪያ መጽሃፍት ውስጥ አንብቦው መልመጃ እንዲሰሩ ሲታዘዙ ተነሳሽነት አይታይባቸውም

ጥያቄ

7. የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማወቅ በግል ወይም በቡድን በመሆን በትምህርት ቤት ደረጃ የተሰሩ ጥናታዊ ስራዎች አሉ? ከሉስ ያስገኙትን ውጤት እንዴት ይገልፁታል?

መልስ

እንደማስተምርበት ትምህርት ቤት በዚህ ርዕስ ላይ የተሰራ ጥናት የለም እንደግልም እንደቡድንም የተሰራ ስራ የለም፡፡ እንደ ትምህርት ቤት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት የማጠቃለያ ፈተና በሚሰጥበት ወቅት ከምናወጣው ምንባብ ውጭ የተሰራም ሆነ የሰራሁት ስራ የለም፡፡

ጥያቄ

8. የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የንባብ ፍጥነት ለማዳበር ምን ቢደረግ ይሻላል ይላሉ?

መልስ

ዋናው የንባብ መሰረት የሚጀመረው ከቤት ውስጥ ስለሆነ ህፃናቱን ወደ ት/ቤት ስንልክ አያይዘን በቤት ውስጥ አገዛ ማድረግ መጽሐፍትን ገዝተን እያነበብንላቸው ፍላጎታቸውን ማነሳሳት ፣ በ1ኛ ደረጃ ት/ቤት ሲማሩ ፊደላት በሽምደዳ ሳይሆን በአይነት ለይተው እንዲያውቋቸው በሚያስችል መልኩ ቢሰራ በወላጅ በትምህት ቤትና በመምህራን መካከል የተሸለ ግንኙነት መፍጠር ወላጅ በልጁ ብቃት ዙሪያ ከመምህራን ጋር ተቀራርቦ የመነጋገር ልምድ ቢዳብር ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ላይ ማሻሻያ ቢደረግ ተሸለ ነገር ላይ እንደርሳለን የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

ጥያቄ

9. የንባብ ትምህርት ለማዳበር የሚቻለው በቋንቋ መምህራን ላይ ብቻ ሳንወሰን የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን በሚያስተምሩ መምህራን የጋራ ጥረትና ርብርቦሽ ነው ቢባል በተሰነዘረው ሃሳብ ይስማማሉ?

መልስ

አዎ በሚገባ እስማማለሁ ሀላፊነቱን በቋንቋ መምህራን ላይ ብቻ በመጣል ችግሩን ልንወጣ አንችልም፡፡ የሁሉን ትምህርት ማለትም በጽሁፍ ሰፍሮ የሚገኘውን መልዕክት ለመረዳት የሚቻለው በምንባብ አማካይነት ስለሆነ ማንበብ እስካልቻለን ድረስ መልዕክትን መረዳት ስለማንችል ሁሉም መምህር ለተማሪዎች ንባብን በማስታጠቅ በኩል ከፍተኛ ሃላፊነት አለበት እላለሁ፡፡

ጥያቀ

10. የተማሪዎችን የንባብ ችግር ለመቅረፍ ከተማሪው ወላጅ ጋር ተገናኝቶ በመወያየት በኩል ምን ያህል ተጉዘዋል?

መልስ

ከተማሪዎ ወላጆች ጋር አልፎ አልፎ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ እገናኛለሁ፡፡ ሆኖም በተጠየኩት ጥያቄ ላይ ተንተርሶ የጎላ ውይይት ባላደርግም ተማሪዎች የተሰጣቸውን የቤት ስራ ሳይሰሩ ሲቀር ከትምህርት ቤት መቅረት ሲያበዙ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እያሉ ክፍለ ጊዙውን ሳይጠቀሙበት ሲቀር በመሳሰሉት ላይ ተገናኝቼ እወያያለሁ .. እግረ መንገዴንም የንባብ ችግር ያለባቸው መሆናቸውን በመጠቆም ችግሩን በመቅረፍ በኩል ተገቢ ጥረት እንዲያደርጉ አበረታታለሁ.፡፡

ጥያቄ

11. ተጨማሪ አስተያየት ካለዎች ገለፁ?

መልስ

ለመምህራን በማስተማር ስነዘዴ ዙሪያ ላይ ተከታታይ ስልጠና ቢሰጥ ለማስተማር ሪያነት የሚዘጋጅ መጽሃፍቶች ውስጣዊ ይዘታቸው ሳቢና መጣኝ ቢሆኑ ክፍለ ጊዜው በቂ ባለመሆኑ መሻሻል ቢደረግበት፣ ቢቻል ሁሉም ታመሪዎች በኩል የክፍል ደረጃ የሚጀምሩበት ሁኔታ ቢመቻች ጥሩ ነው፡፡